ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 128 ጥር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## «ጥምቀት ማህበራዊ መስተጋብሮች የሚዳብሩበት በዓል በመሆኑ በመተሳሰብ ስሜት ይከበራል»

- አቶ ስለሺ ግርማ
የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ጥምቀት ማህበራዊ መስተጋብሮች የሚዳብሩበትና የአንድነት ስሜት የሚጎሉበት በመሆኑ በአገር አቀፍ ደረጃ በመተሳሰብ ስሜት ይከበራል ሲሉ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ተናገሩ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የጥምቀት በዓል ማኅበረሰቡ በጋራ ከሚያከብራቸው የአደባባይ በዓላት መካከል በመሆኑ የአብሮነትን ስሜት በማጠናከር ረገድ ጉልህ ፋይዳ አለው።

የተለያየ ባህል፣ወግ ልማድ፣ ሃይማኖትና አመለካከት ያላቸው ሰዎች ከተለያየ አካባቢና የዕድሜ ክልል ተሰባስበው አብረው እንዲያከብሩ ዕድል የሚፈጥር በዓል በመሆኑ አገራዊ አንድነት በሚያንጸባርቅ የመተሳሰብ እሴት ይከበራል ብለዋል።

«ጥምቀት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በክልሉ በበጋ መስኖ ለማልማት ከታቀደው መሬት እስካሁን 80 በመቶ በዘር ተሸፍኗል

- በበጋ ስንዴ ልማት ከ748 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ ለማልማት ከታቀደው 208ሺህ ሄክታር መሬት እስካሁን ድረስ 80 በመቶ በዘር መሸፈኑን የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። 20ሺህ ሔክታር መሬትን በበጋ ስንዴ በማልማት ከ748ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ እየተሠራ እንደሆነም ተገልጿል፡፡

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በበጋ መስኖ ለማልማት ከታቀደው 208ሺህ ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን ድረስ 80በመቶ በዘር መሸፈን ተችሏል። ከጥር አንድ እስከ 10 ቀን 2015ዓ.ም ባለ ጊዜ ውስጥም የዘር ሥራ ለማጠናቀቅ የድጋፍና ክትትል ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ፡፡

በዘድሮው በበጋ መስኖ ከሚለማው መሬት ውስጥ 188ሺህ ሄክታሩ መሬት ላይ የሚለሙት አትክልት፣ ፍራፍሬና የተለያዩ ሰብሎች መሆናቸውን ገልጸው፤ ክልሉ በበጋ ስንዴ 20ሺህ ሔክታር መሬት በማልማት ከ748ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ እየተሠራ መሆኑን



አቶ ኡስማን ሱሩር

ተናግረዋል፡፡

በበጋ ስንዴ ልማት ከሚሸፈነው 20ሺ ሄክታር ውስጥ እስካሁን ከ9ሺህ 500 ሔክታር መሬት በላይ በስንዴ ዘር እንደተሸፈነ አመልክተው፤ የተሻለ ምርት ለማግኘትም 90 በመቶ የሚሆነውን መሬት ትራክተር በመጠቀም የእርሻ ዝግጅት መደረጉንና እንደ አካባቢው ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር መጠቀም መቻሉን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፤ የበጋ ስንዴ ልማት በክልል እና በአገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ

በክልሉ በበጋ መስኖ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «የተገኘውን ሰላም አብዝተን ልንጠብቀውና ዘላቂ ልናደርገው ይገባል»

- ሀጂ አወል አርባ

ገጽ 4

## ጎንደር ከተማ በጥምቀት በዓል እስከ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ እንግዶችን ለመቀበል ተዘጋጅታለች

ገጽ 4






















ዶክተር አራርሶ ገረመው

# ክልሉ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ለማድረግ እየሠራ ነው

**ክብረአብ በላቸው**

አዲስ አበባ፡- ለሙስናና ብልሹ አሠራር በር ሲከፍት የቆየውን የመንግሥትን የግዥ ሥርዓት ለማዘመን እና ሙሉ ለሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ለማከናወን የሚያስችሉትን ተግባራት እያከናወነ መሆኑን የሲዳማ ክልል ፋይናንስ ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አራርሶ ገረመው፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሁን ባለው የግዥ ሥርዓት የሚከናወኑ ግዥዎች ለሙስናና ብልሹ አሠራሮች የመጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ ነው። የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ከዚህ ቀደም በነበረው አሠራር የሚባክነውን የመንግሥትንና የሕዝብ ሀብት በመዳን ግልፅነት የሰፈነበት ሥርዓት ለመዘርጋት ሚናው የጎላ እንደመሆኑ፤ በክልሉ የሚከናወኑ ግዥዎችን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ የግዢ ሥርዓት ለመፈጸም የሚያስችለውን ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

በጨረታ ሂደትና በተለያዩ መንገዶች አለአግባብ ተጠቃሚ የነበሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ይህን አሠራር እንደማይፈልጉ የተናገሩት ዶክተር አራርሶ፤ ነገር ግን እነርሱ ባይፈልጉትም አሠራሩን ተግባራዊ ከማድረግ ወደ ኋላ እንደማይሉ ገልፀዋል። የተለያዩ የዓለም አገራት ይህን አሠራር ከሃያ አመታት በፊት መጠቀም እንደጀመሩ ተናግረው፤ እንደ አገርም ይሄ አሠራር ወደሥራ እየገባ በመሆኑ አሁን ላይ ክልሉ በደረሰበት ደረጃ አሠራሩን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እያደረገ መሆኑንም ገልፀዋል።

እንደ ዶክተር አራርሶ ማብራሪያ፤ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት አሠራር አሁን ባለው ጥናት መነሻ ከአርባ እስከ ሃምሳ በመቶ ሙስናን እንደሚቀንስና የፋይናንስ ኦዲትን በማስቀረት ጭምር የክዋኔ ኦዲት ብቻ እንዲኖር በማድረግ አሠራሩን ቀልጣፋ የሚያደርግ ነው። እንደ ክልልም ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ቁመና በመፍጠር ከኢፌዴሪ ግዥና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ጋር ሥራውን ለማስጀመር ጥረት እያደረጉ ይገኛል።

ሥርዓቱ፣ በተለይም የጨረታ አሠራር ከሰው የእጅ ንክኪ ነፃ በማድረግ ማንኛውም ባለጉዳይ በስልክ ወይም በኮምፒዩተር ባለበት ሆኖ ከምዝገባ እስከ ክፍያ ያሉ ሂደቶችን በማጠናቀቅ ዘመናዊና ከሙስና የፀዳ አሠራር እንዲኖር የሚያደርግ እንደመሆኑ ክልሉ ለዚህ አሠራር እውን መሆን በትኩረት እየሠራ መሆኑን ነው ዶክተር አራርሶ ያስረዱት።

በአሁኑ ሰዓት እንደ ክልል ሃያ ወረዳዎች ወደዚህ ሥርዓት የሚገቡበትን መስፈርት ጨርሰናል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በክልል ደረጃ ደግሞ ከሃያ ሦስት ተቋማት በላይ ወደዚህ አሠራር በማስገባት ምን ያክል ወጪ ወጣ፣ በምን ምክንያት ወጣ፣ የሚለውን ለመለየትና የወጪና ገቢ ቁጥጥርና ክትትል ሕግና ሥርዓትን ብቻ ተከትሎ እንዲሄድ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነም ተናግረዋል።

ይህ ደግሞ አሁን ላይ ሕዝቡ ከብልሹ አሠራር፣ ከሀብት ብክነት እና ተያያዥ የግዥ ሥርዓቱ ችግሮች ዙሪያ ሕዝቡ ለሚያነሳቸው ሮሮዎች መልስ ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን የጠቆሙት የቢሮ ኃላፊው፤ ሁሉም ለዚሁ አሠራር ራሱን ማዘጋጀት እንዳለበት አሳስበዋል። በቢሮና በተቋማት የሚሠራ ማንኛውም አመራርም ሆነ ባለሙያ ይህንን ቴክኖሎጂ መጠቀም እንደሚገባው አሳስበዋል።

ከኅብረተሰቡ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመፍታትና በፋይናንስ ዘርፉ የሚስተዋለውን ሙስናና ብልሹ አሠራር ለመቀነስ በቁርጠኝነት እየተሠራ መሆኑንም አስረድተዋል።

# የጎንደር ከተማን የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት እየተሠራ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- የጎንደር ከተማና አካባቢውን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ በቆላ ድባና አንገረብ ግድብ አካባቢ የአምስት የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፕሮጀክቶች እንደሚከናወኑ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ክትትልና ድጋፍ ዴስክ ኃላፊ አቶ ኃይማኖት በለጠ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአካባቢዎቹን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ የሚረዱትን አምስት የውሃ ጉድጓድ ፕሮጀክቶችን ለማስጀመር ከአካባቢው አስተዳደር ጋር በጥምረት እየተሠራ ይገኛል።

በመጀመሪያው ዙር በቆላ ድባና አንገረብ ግድብ አካባቢዎች በእያንዳንዳቸው ስፍራ አንድ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ይቆፈራል። በአካባቢዎቹ የተሻለ የከርሰምድር ውሃ አቅም ያለበትን በመለየት ደግሞ ተጨማሪ ሦስት የውሃ ጉድጓድ ፕሮጀክቶችን ለመጀመር ዕቅድ ተይዟል ብለዋል።

በአጠቃላይ በአካባቢዎቹ ለሚከናወኑት አምስት የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፕሮጀክቶች ከ115 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት እንደተመደበ አቶ ኃይማኖት አስታውቀዋል።

የፌዴራል መንግሥት በቀጣይ ለሚገነቡት ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ማስቆፈሪያ የሚውሉ ማሽኖችን አቅርቦት እያደረገ ይገኛል ያሉት አቶ ኃይማኖት፤ ማሽኖቹን ወደየፕሮጀክት ስፍራቸው ለማድረስ የቅድመ ዝግጅት ሥራው ተጠናቋል ብለዋል።

የዞኑን ስር የሰደደ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ ከዚህ ቀደም የጥልቅ ጉድጓድ ቁፍሮ ሥራ የተጀመረባቸው ሦስት ቦታዎች እንደነበሩ አቶ ኃይማኖት ጠቁመው፤ በአማራ ክልል መንግሥት በኩል የሁለት ጉድጓዶች ቁፋሮ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የፌዴራል መንግሥት በበኩሉ በአካባቢዎቹ ባለ 500 ሜትር ጥቅል የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እያከናወነ ይገኛል። የቁፋሮ ሥራው ከ300 ሜትር በላይ በመድረሱ ሂደቱ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

የውሃ ጉድጓዱ ካለው ስፋት በተጨማሪ አለታማ ድንጋይ ሲያጋጥም ሂደቱን ሊያዘገየው እንደሚችል ጠቁመው፤ በመሀል ሥራው የተለየ ችግር ካልገጠመው በስተቀር የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮው በአንድ ወር ውስጥ ሊያልቅ እንደሚችል አመላክተዋል።

ከዚህ ባለፈ ቀድሞ ተሠርተው ያለአገልግሎት ታሽገው የነበሩት የውሃ ጉድጓዶችን በተለይም የአንገረብ ግድብ ፕሮጀክትን እንዲሁም ሌሎች የተጀመሩ ግድቦችን በሙሉ አቅም ለማጠናቀቅ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ችግሩን ለመቅረፍ ያለአገልግሎት ተዘግተው የቆዩ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶችን በመጠገንና የማሻሻያ ሥራ በማከናወን መልሰው የንፁህ መጠጥ ውሃ እንዲሰጡ ተደርጓል ሲሉ አቶ ኃይማኖት ገልጸዋል።

በተጨማሪ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ችግሮች የነበረባቸውን የውሃ መሳቢያ ጄኔሬተሮችንና የውሃ ማስተላለፊያ መስመሮችን በመቀየር ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል ሲሉ የተናገሩት አቶ ኃይማኖት፤ በዚህም የአካባቢዎቹን የውሃ አቅርቦት ለማሻሻል የሚረዳ ሥራ መከናወኑን ጠቁመዋል።

የማዕከላዊ ጎንደርን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ለማሳደግ ቀድሞ የተጠኑ ሰነዶችን በመከለስና የዲዛይን ማሻሻያ በማድረግ ከዩኒቨርሲቲ ምሁራንና አማካሪዎች ጋር የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። በቀጣይም ሰነዶቹን መሠረት አድርጎ በጀት የማፈላለግና ተጨማሪ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አቶ ኃይማኖት አስታውቀዋል።

# ጠንካራ አገር ተረካቢ ትውልድ ለመፍጠር ልጆችን በእውቀት ኮትኩቶ ማሳደግ ላይ ትኩረት መስጠት ይገባል

**በስጥሻቸው ልዑልሰገድ**

አዲስ አበባ፡- ጠንካራ አገር ተረካቢ ትውልድ ለመፍጠር ልጆችን በእውቀት ኮትኩቶ ማሳደግ ላይ ትኩረት መስጠት ይገባል ሲሉ ደራሲ ጌታቸው በለጠ አመለከቱ። ዛሬ በሕፃናት ላይ የሚሠሩ ሥራዎች የነገዋን ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ስለሚወስን ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል።

ደራሲ ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በአሁኑ ጊዜ ለሕፃናት እየተሰጠ ያለው ትኩረት አናሳ ነው። ትምህርት ሚኒስቴር ራሱ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተገቢውን የሕፃናት ፕሮግራም ወይም የሙዓለ ሕፃናት ፕሮግራም አልነበረውም። ይልቁንስ የሕፃናት ትምህርት በትምህርት ሚኒስቴር ሳይሆን በግለሰቦች ሲመራ መቆየቱ መንግሥት ለጉዳዩ የሰጠው ትኩረት አናሳ እንደነበር ያሳያል።

ዛሬ ላይ በሕፃናት አዕምሮ ላይ የሚሠራው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ሥራ ነገ እውን እንድትሆን ለምንፈልጋት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ አበርክቶ እንዳለው የገለጹት ደራሲው፤ በመሆኑም እንደ አገር በሕፃናት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግና በተለይ ሕፃናት ላይ ያተኮሩ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን በስፋት ማዘጋጀት ጠቃሚ መሆኑን መክረዋል።

አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የምታገኘው ድጋፍ አልሚ ምግቦች ድጋፍ ብቻ ሳይሆን የሕፃናት መጽሐፍ ጭምር መሆኑን ያነሱት ደራሲው፤ በተመሳሳይ መልኩ የተለያዩ የውጭ ድርጅቶች ወደ አገሪቱ በመግባት በሚፈልጉት ዓላማ የሚያዘጋጁት የሕፃናት መጽሐፍት በይዘትና በአቀራረባቸው ከጥቅማቸው ጉዳታቸው እንደሚበልጥ አስገንዝበዋል።



ደራሲ ጌታቸው በለጠ

ከውጭ የሚገቡ መጽሐፍትም ሆነ በውጭ የሚታተሙ ጽሑፎች ሕፃናት የራሳቸው ባህል፣ ወግ እና ሥርዓት ወደ ጎን በመተው የባዕድ ላይ እንዲጠመዱ ያስገድዳቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

ዳሩ ግን በተለያዩ ጊዜያት ከውጭ ለሚገቡ የልጆች መጽሐፍት ወግና ባህሉን በጠበቀ መልኩ አገር ውስጥ ለማምረት የህትመት ዋጋ በዚህ ልክ መጨመሩ ተገቢ አለመሆኑን የጠቀሱት አቶ ጌታቸው፤ ትውልድን ለመታደግ ከሕትመት ከሚገኘው ትርፍ መተው የግድ ይላል ብለዋል።

እንደ ደራሲ ጌታቸው ማብራሪያ፣ በርካታ ልጆች ዕድሜያቸውን የሚመጥኑና በልካቸው የተጻፉ መጽሐፍትን እንደልብ ባለማግኘታቸው ወደ ኢንተርኔቱ አዘንብለዋል። ይህ መሆኑ ደግሞ ሕፃናት በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ዕድሜያቸውን የማይመጥኑ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን እንዲመለከቱና አለፍ ሲልም ያዩትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል።

በተለይ ትውልድ በሥነ-ጽሑፍ ሲገፋና የሚመገበውን የእውቀት ገበታ መንፈግ ሲጀምር በአገር ላይ የሚደርሰው ጉዳት እጅግ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለቆ ከወጣና አፄ ኃይለሥላሴ ወደ አገር ከተመለሱ በኋላ ወዳጆቻቸውን ሹማምንታቸውን በመሰብሰብ ለሕፃናት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ላይ ምክክር ማድረጋቸውን ያወሱት ደራሲ ጌታቸው፤ በዚሁ መሠረት የመጀመሪያው የሕፃናት መጽሐፍ በ1934 ዓ.ም «ተረትና ምሳሌ» በሚል ርዕስ በከበደ ሚካኤል ተጽፎ መታተሙን ተናግረዋል። ከዚያ በኋላ በርካታ ደራሲያን ለሕፃናት የሚሆኑ መጽሐፍትን ማዘጋጀት መጀመራቸውን አውስተዋል።

አሁን ላይ የትኩረት ማነስ ችግር እንዳለ ሆኖ ውስን ደራሲዎች የሕፃናት መጽሐፍት በግላቸው ለማዘጋጀት ጥረት ቢያደርጉም የህትመት ዋጋ መናር ችግር መሆኑን አቶ ጌታቸው ገልጸዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የማህበራዊ ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ አቶ ኡመር ኢማም በበኩላቸው፣ ከዚህ ቀደም ለሕፃናት የተሰጠው ትኩረት አናሳ ከመሆኑም በላይ በተለይ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ከመንግሥት ይልቅ የግሉ ዘርፍ በትኩረት ሲሠራ መቆየቱን አውስተው፤ አሁን ግን በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ለሕፃናት ትምህርት ከሌሎች እርከኖች እኩል ትኩረት መሰጠቱን አመልክተዋል።

ለሕፃናት ትምህርትም ከመማሪያ መጽሐፍ፣ ከመምህራን እና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችን ጨምሮ በጀት ተመድቦለት ከሌሎች ትምህርት እኩል በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በቀጣዩ ዓመት ተግባራዊ እንደሚደረግም ገልጸዋል።

# ዳያስፖራው በዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ላይ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ ይገባዋል

**ሙሳ ሙሐመድ**



**ዶክተር ሙሐመድ እንድሪስ**

አዲስ አበባ፡- ዳያስፖራው በዕውቀትና ክህሎት ሽግግር ላይ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ እንደሚገባው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሙሐመድ እንድሪስ እንደገለጹት፣ ዳያስፖራው ማህበረሰብ በውጭ አገራት ያገኘውን ዘርፈ ብዙ ዕውቀት፣ ክህሎትና የለውጥ ሃሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚችለውን ሁሉ ጥረት ማከናወን አለበት።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ በተለይ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ፣ በፋይናንስና ኢኮኖሚ እንዲሁም በማህበራዊ ችግር ፈቺ ጉዳዮች ላይ የሰሩ ዳያስፖራዎች ዕውቀታቸውን ለኢትዮጵያውያን የሚያስተላልፉበትን መንገድ ይበልጥ ማሳደግ ይኖርባቸዋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል ዳያስፖራው በዕውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት ውስጥ እንዲሳተፍ ማደረግ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህም ጋር በተያያዘ ዳያስፖራውን ማህበረሰብ ያሳተፉና በሀገር ውስጥ ልዩ ልዩ ተቋማትን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የአቅም ግንባታ የስልጠና መድረኮች እየተዘጋጁ መሆኑን ጠቁመዋል።

በቀጣይም በጥናት በተለዩ ጉዳዮች ላይ በአገር ውስጥ ያለውን የስልጠና ፍላጎትና ክፍተት ዳያስፖራው ማህበረሰብ እንዲሞላው የሚረዱ ሥራዎች ይከናወናሉ። ዳያስፖራው አገሩን ለመጥቀም ያለውን ፍላጎትና አቅም በሚመጥን መልኩ የማስተባበር ሥራ እንደሚከናወን ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

ቀጣይ ለዕውቀትና ክህሎት ሽግግር የሚረዱ ስልጠናዎች ከዳያስፖራው ማህበረሰብ ጋር በመሆን ሲከናወኑ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከፈጠራና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በስፋት እንደሚዳሰሱ ጠቁመዋል።

በሰለጠነው ዓለም እየተገበሩ ያሉ ጠቃሚ አሠራሮችንና የፈጠራ ሃሳቦች ላይ የዕውቀት ሽግግር በማከናወን ለአገር ግንባታ መጠናከር የሚረዱ ተጨባጭ ውጤቶችን ለመቀመር ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፣ ወደ አገር የሚመጡትን ዳያስፖራዎች ሙያ፣ ልዩ ክህሎትና አቅም በመለየት በተለያዩ የአገሪቷ አካባቢዎች ላይ ዕውቀትና ክህሎታቸውን ለማህበረሰቡ እንዲያሸጋግሩ የሚረዱ የትስስር መድረኮችም መከናወን ጀምረዋል።

በአገር ውስጥ እየተፈጠረ ያለውን ሁኔታ ተከትሎ ከተለያዩ የዓለም አገራት የሚኖሩና በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ዳያስፖራዎች በቀጣይ ወደኢትዮጵያ ይመጣሉ። ዳያስፖራዎችም በሥራ ዘመናቸው ያካበቱትን ዕውቀትና ክህሎት በአገር ውስጥ ጥቅም ላይ ለማዋል ዝግጅት አድርገው ሊመጡ ይገባል ብለዋል።

# በክልሉ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ሕዝቡ ትኩረቱን በልማት ሥራ ላይ እንዲያደርግ አድርጓል

**ጽጌረዳ ጫንያለው**


**አቶ አቢዮት አልቦሮ**

አዲስ አበባ፡- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ከታጣቂዎች ጋር ያደረገው የሰላም ስምምነት ኅብረተሰቡ ትኩረቱን በልማቱ ላይ እንዲያተኩር እንዳደረገው የክልሉ ሰላም ግንባታና ጸጥታ ቢሮው አስታወቀ።

የክልሉ ሰላም ግንባታና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ አቶ አቢዮት አልቦሮ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ ሁልጊዜ በጦርነትና በግጭት ዘላቂ ሰላምን ማምጣት አይቻልም። ሰላምም ሊረጋገጥ አይችልም። ስለሆነም ሰላምን ለማምጣት ችግሮችን በውይይትና በስምምነት መፍታት ያስፈልጋል። ክልሉም ይህንን በመረዳቱ ችግሮችን በሰላማዊ ድርድሮች ለመፍታት ከታጣቂ ቡደኖቹ ጋር ተስማምቷል። በድርድሩ መሠረትም ለታጣቂ ቡድኖቹ መንግሥት ማድረግ ያለበትን እንዲያደርግ ቃል ገብቷል። ስለዚህም ቃሉን ለማክበር ሥራዎችን ጀምሯል።

የክልሉ መንግሥት የሰላም ስምምነቱ ቀጣይነት እንዲኖረውም ቁርጠኛ ሆኖ በርካታ ተግባራትን እየከወነ እንደሆነ ያነሱት አቶ አቢዮት፤ ኅብረተሰቡም ሙሉ ትኩረቱን በልማት ሥራዎች ላይ እንዲያደርግ ትልቅ መሠረት መጣሉን ተናግረዋል።

መንግሥት በስምምነቱ መሠረት ለሰላም ተመላሾች እንደየፍላጎታቸው በተለያዩ ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። በእርሻ ሥራ ላይ እንሰማራለን ላሉት አካላት ለእርሻ ሥራቸው የሚያግዙ እንደ ትራክተር ዓይነት መሣሪያዎችን ገዝቶ የመስጠት ሥራ ተሠርቷል። በሌላ በኩልም በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ ቦታና ገንዘብ አግኝተው ወደ ሥራ እንዲገቡም አመቻችቷል።

የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን የሰላም ተመላሾችም ወደ ሥራ የሚገቡበትና እንደክልልም ሆነ እንደ አገር አበርክቶ የሚያደርጉበትን መንገድ ክልሉ እየፈጠረ ይገኛል ያሉት አቶ አቢዮት፤ በተለያዩ የሥራ መስክ ላይ ተሰማርተው የነበሩትን ሳይቀር ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ የማድረግና ሕይወታቸውን እንዳለፈው እንዲመሩ የማስቻል ሥራ መከናወኑን አንስተዋል።

ወደ ንግድ ሥራ መግባት እንፈልጋለን ያሉትንም ቢሆን እንደየፍላጎታቸው የማገዝ ተግባር እያከናወነ እንደሆነም የጠቆሙት አቶ አቢዮት፤ መንግሥት እንደመንግሥት ቃል የገባውን እየተገበረ ይገኛል።

እንደ አቶ አቢዮት ገለጻ፤ ከስምምነቱ በኋላ ብዙ ነገሮች እየተለወጡ ናቸው። ከጅማሮው ብዙ ትምህርት የተገኘበትና የአስተሳሰብ ለውጥን ያመጣም ነው። ማህበረሰቡም ሆነ ታጣቂዎቹ የጦርነትን አስከፊነት አይተውበታል፤ ተረጋግቶ የመሥራትን ዋጋም እየተረዱት ይገኛሉ። ስለዚህም ይህንን በዘላቂነት ለማስቀጠል ደግሞ ሁሉም የድርሻውን ማድረግ ይኖርበታል።

ችግሮች መቼም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ ሊጠፉ አይችሉም። ስለሆነም የውይይትን ዋጋ አውቆ መጠቀም ላይ ሁሉም ርብርብ ማድረግ እንዳለበት ያሳሰቡት አቶ አቢዮት፤ በክልሉ አሁን ያለው ሁኔታ መንግሥትን ከግጭት ወደ ልማት ፊቱን እንዲያዞር አድርጎታል ብለዋል።

ታጣቂዎችም ሰላምን በመምረጣቸው ተጠቃሚነታቸው እየተረጋገጠ ነው። ስለሆነም ሌሎች ምርጫቸውን ብጥብጥ የሚያደርጉ አካላት ከዚህ ሁኔታ መማር አለባቸው። ከድርጊታቸው ተቆጥበውም መልካሙን መንገድ ሊመርጡ ይገባል። በሰላም ራሳቸው ጠቅመው አገራቸውንና ሕዝባቸውን ለማገልገልም ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል። አሁንም አገርን እናተራምሳለን ብለው በየጫካው ያሉ አካላት ምርጫቸውን ሊያስተካክሉ ይገባል ብለዋል።


ወይዘሮ እናትነሽ ታመነ

# በመዲናዋ በስድስት ወራት ከአንድ ሺ 500 በላይ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በስድስት ወራት አንድ ሺ 564 ባለሀብቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መውሰዳቸውን አስታወቀ። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የዕቅድና በጀት ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክተር ወይዘሮ እናትነሽ ታመነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ የከተማዋን ኢንቨስትመንት ፍሰት ለመጨመር የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ነው። በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ አንድ ሺ 564 ባለሀብቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተዋል ብለዋል።

አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ከመሳብ ባለፈ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው ወደ ሥራ ያልገቡትን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ወደ ሥራ የማስገባት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ባለፉት ስድስት ወራት 99 ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ መቻሉን ጠቁመዋል።

በከተማዋ ያሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለባለሀብቶች ማስተዋወቅ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለመጨመር ጉልህ ሚና እንደሚጫወት የጠቀሱት ወይዘሮ እናትነሽ፤ ኮሚሽኑ አዳዲስ ባለሀብቶች በከተማዋ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚያበረታታና መሰማራት ስለሚፈልጉበት ዘርፍ ግልጽነት የሚፈጥር የአዋጭነት ጥናት በማስጠናት ጥናቱን በሶፍት እና በሀርድ ኮፒ እንዲሰራጭ እያደረገ ነው። 44 ጥናቶችን በውጭ አጥኚዎች ማስጠናቱንና ተጨማሪ 10 ጥናቶችንም በውስጥ አቅም በማስጠናት ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህም ባለፉት ስድስት ወራት ለ2 ሺ 863 ባለሀብቶች መረጃውን ማድረስ መቻሉን ጠቁመው፤ መረጃ አግኝተው ወደ ተቋሙ ከመጡት ውስጥ ሁለት ሺህ የሚሆኑት አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ለማድረግ ታቅዶ አንድ ሺ 564 ባለሀብቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተዋል።

የተሸከርካሪ ማበረታቻ መቆም፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የመሬት አቅርቦት አለመኖር፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ አለመረጋጋት ባለሀብቶች በሚፈለገው ልክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዳይወስዱ ምክንያት መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየትና የአሠራር ማንዋሉን በአዲስ በማሻሻል ባለሀብቶች የሚያነሷቸውን ችግሮች ለመቅረፍ እየተሠራ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በተጨማሪም የሚያስመዘግቡት ካፒታል መጠን ከባንክ 30 በመቶ ባንክ ስቴትመንት እና ፕሮጀክት ፕሮፖዛል እንዲያመጡ ይጠየቅ የነበረውን በማስቀረት ሂደቱን ግልጽና ቀልጣፋ ማድረግ መቻሉን ገልጸው፤ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመውሰድ የሚያስችሉ ሥራዎችን በአንድ ማዕከል በማዋቀር አንድ ባለሀብት በ20 ደቂቃ ውስጥ አገልግሎት አግኝቶ እንዲመለስ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል።

የኢንቨስትመንት ሥራው ከባለድርሻው አካላት ጋር በቅንጅት የሚሠራ ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ባለሀብቱ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ ከሚሠራው ሥራ ጎን ለጎን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሥራውን በባለቤትነት እንዲሠራ የሚያስችል የኢንቨስትመንት ፎረም ባለድርሻውን ያቀፈ እና በቅንጅት የሚሠራበት ሰነድ እየተዘጋጀ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

ዜና



# ጎንደር ከተማ በጥምቀት በዓል እስከ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ እንግዶችን ለመቀበል ተዘጋጅታለች

ታደሰ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ጥንታዊቷ የጎንደር ከተማ የጥምቀት በዓል ላይ ለመታደም የሚመጡ ከ750 ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን የጎንደር ከተማ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ገለጸ።

የጎንደር ከተማ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ ጥሩዬ አትክልት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በዓለም ላይ በጥምቀት በዓል አከባበር የምትታወቀው ጥታዊቷ ጎንደር ከተማ ጥምቀትን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ዝግጅቷን ከመስከረም ወር ጀምራ ስታደርግ ቆይታለች።

ለበዓሉ ወደ ከተማዋ ጥሪ ተደርጎላቸውና ለጉብኝት የሚመጡ ከ750 ሺህ እስከ 1 ሚሊዮን የሚደርሱ ታዳሚዎች ተገቢውን የመኝታ፣ የትራንስፖርትና ልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲያገኙ የዝግጅት ሥራ መሠራቱን ወይዘሮ ጥሩዬ ጠቅሰው አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ እንዲያገኙ ክትትልና ቁጥጥር ይደጋል ብለዋል።

የበዓሉ ታዳሚዎች ባህረ ጥምቀቱን ሲያከብሩና ከአከባበሩ በኋላ የሚያርፉበት ቦታ አጥተው ለተለያዩ ችግሮች እና እንግልት እንዳይዳረጉ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተሠራ መሆኑንና በከተማዋ ያሉ ባለኮከብ ሆቴሎች ባለሀብቶች ያላቸውን አቅም አሟጠው በመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋና በጥሩ መስተንግዶ እንግዶችን እንዲቀበሉ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ሲሉ አብራርተዋል።

በተጨማሪም በከተማዋ ከሚገኙ የዘመናዊ ሆቴል ባለሀብቶች ጋር ውይይት እንደተደረገና ከነሱ ጋርም በቅንጅት በመሥራት ለአስተናጋጆች የሥነ- ተግባቦት ትምህርትና የእንግዳ አቀባበል ልዩ ስልጠና እንደተሰጠ ወይዘሮ ጥሩዬ ጠቅሰው ሰልጣኞችም ባገኙት እውቀትና ልምድ እንግዶችን ለመቀበል ዝግጁ ናቸው ብለዋል።

ይታደማል ተብሎ የታሰበው ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ካሉት ሆቴሎችና ፔንሲዮኖች በተጨማሪ ዘመናዊ ድንኳኖች መዘጋጀታቸውን እንዲሁም ኅብረተሰቡ ባለው የእንግዳ አቀባበል ባህል መሠረት አቅሙ የፈቀደውን ያህል እንግዳ እንዲቀበልና ባህሉን፣ ወጉን እና እሴቱን ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ለሚመጡ እንግዶች እንዲያስተዋውቅ ይረዳዋል ሲሉ አብራርተዋል።

በዘላቂነት ጎንደርን የቱሪስት መዳረሻ ማዕከል ለማድረግ ያላትን ታሪክ፣ ባህል፣ ወግ እና ሥርዓት ለዓለም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ወይዘሮ ጥሩዬ ገልጸዋል።

በከተማዋ ሳምንት እየተከበረ በሚቆየው የጥምቀት በዓል የተለያዩ ክንዋኔዎች እንደሚቀርቡና አርቲስት ማሪቱ ለገሰን ጨምሮ ሌሎች አንጋፋ አርቲስቶች በበዓሉ ላይ እንደሚታደሙም ኃላፊዋ ጠቁመዋል።

በዘንድሮው የጥምቀት በዓል ከወትሮው ለየት ለማድረግ ከተሠሩ ሥራዎች ውስጥ «ኅብረ ዝማሬ» በሚል መሪ ቃል የመጀመሪያ ጎዳና ላይ የአዝማሪ ፌስቲቫል፣ የሚስ አማራ ቁንጅና ውድድር፣ ሙዚቃ በመሰንቆ፣ የእራት ግብዣ እና የአፄ ቴዎድሮስ 204ኛ የልደት በዓል አከባበር እንደሚገኙበት ገልጸዋል።

ለበዓሉ ወደ ከተማዋ የመጡ እንግዶች በዓሉን በሰላም አክብረው ወደየመጡበት ቀዬ በሰላም እንዲመለሱ የፀጥታ አካላት በንቃት እንደሚሠሩና ኅብረተሰቡም በሰፈር አደረጃጀት በመደራጀት እና ከሕግ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት እንግዶችን በፍቅር ተቀብሎ በፍቅር ለመሸኘት የሚያስችል ሥራ መሠራቱን ተናግረዋል።

# ሕወሓት ከባድ የጦር መሣሪያዎችን ማስረከብ መጀመሩ ለሰላም ስምምነቱ ዘላቂነት ዋስትና ነው

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት የነበሩትን ከባድ የጦር መሣሪያዎች ለአገር መከላከያ ሰራዊት ማስረከቡ በፕሪቶርያ ለተካሄደው የሰላም ስምምነት ዘላቂነት ዋስትና እንደሚሆን በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ተናገሩ።

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህሩ አቶ ሰለሞን ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሁን ላይ ሕወሓት በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ መከላከያ ሰራዊት ብቻ መኖር እንዳለበት አምኖ የጦር መሣሪያዎቹን ለአገር መከላከያ ሰራዊት ማስረከቡ ለአገሪቱ ዘላቂ የሰላም ዋስትና ማረጋገጫ ነው።

ሕወሓት ከባድ መሣሪያዎችን ማስረከቡ የኢትዮጵያን ሕገ-መንግሥታዊ ሉአላዊነት ለማረጋገጥ ትልቅ እመርታ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት የታጠቁ ኃይሎች መኖር እንደሌለባቸውም ገልጸዋል።

ከባድ የጦር መሣሪያዎች የማስረከቡ ድርጊት ሕወሓት የተደረገውን የሰላም ስምምነት እንዳመነበት የሚያሳይ ነው ያሉት መምህሩ፣ የጦር መሣሪያውን ሳያስረክብ የተደረገ የሰላም ድርድር ዘላቂ አይሆንም፣ የአገሪቱ ሰላምም ዘላቂ ዋስትና አይኖረውም ሲሉም አክለዋል።

ሕወሓት የጦር መሣሪያዎቹን ለአገር መከላከያ ሰራዊት ማስረከቡ ለኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ለአጎራባች አገራትና ክልሎች ጭምር ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር የሚያስችል፤ በመሆኑ ለዘላቂ ሰላም ወሳኝ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ፤ ድርጊቱ ለአንዳንድ ምዕራባውያን የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን መፍታት እንደሚቻል ማሳያ ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ በራሷ አገር በቀል እውቀት ችግሮቿን መፍታትም እንደምትችል የምናረጋግጥበት ነው ሲሉም መምህሩ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያና ሌሎች አጎራባች አገራት ችግርን ለመፍታት ትልቅ ጥረት ያደረገች አገር ሆና ሳለ የራሷን የውስጥ ችግር መፍታት አለመቻሏ ሲወራ ነበር ያሉት መምህሩ፣ ሕወሓት ትጥቁን ማስረከቡ አገሪቱ የነበራትን ገጽታ እንዲመለስ የሚያደርግና የብዙ ጠላቶችን አፍ የሚያዘጋ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሕወሓት ትጥቁን ለመከላከያ ሰራዊት ማስረከቡ አገሪቱ ሲደርሱባት ከነበሩት የኢኮኖሚ፣ ዲፕሎማሲና ፖለቲካዊ ኪሳራዎች እንድታገግም ከማድረግም አንጻር ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

አቶ ሰለሞን ሲያጠቃልሉም፣ ሕወሓት ከባድ የጦር መሣሪያውን ማስረከቡ ጦርነቱ እንደቆመ የሚያረጋግጥ ነው። ድርጊቱም ለኢትዮጵያ መንግሥት ሁለት እጁን ወደ ልማት እንዲያዞር ትልቅ ማረጋገጫ የሚሰጥ ነው ብለውታል።

# «ጥምቀት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ ያላትን የመከባበር፣ የመቻቻልና የመረዳዳት ባህል እንዲሁም አብሮ የመኖር እሴቷን ለዓለም የምታስተዋውቅበት በዓል መሆኑንም ገልጸዋል።

የጥምቀት በዓል አንዱ ሃይማኖት ከሌላው ሃይማኖት በመተባበርና በመረዳዳት የሚያሳልፉት መሆኑ በቀደሙ ጊዜያት ታይቷል። በተለይ የከተራ ቦታ በማጽዳትና ታቦታቱን በማጀብ እንዲሁም መሰል በጎ ተግባራት በመከወን ረገድ የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮችን ትብብር በማጠናከር ረገድ ትልቅ ጥቅም ተገኝቶበታል ብለዋል።

በቀጣይም ተመሳሳይ የአብሮነት ስሜቶችን የሚያጠናክሩ ሁነቶች ይከናወናሉ። እንደዚህ ዓይነቱ መልካም ተግባራት አገራዊ አንድነት በማጎልበት ለአገራዊ ግንባታ በጎ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በዓሉ ካሉት ማህበራዊ ጠቀሜታዎች ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎቹ በርካታ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢትዮጵያ ከተለያዩ አገራት የሚመጡ ቱሪስቶችን የምታስተናግድበት በመሆኑ የቱሪዝም ገቢን የሚያሳድጉ የማስተዋወቅ ሥራዎች በስፋት መከናወናቸውን አስታውቀዋል።

በጎንደር፣ በአዲስ አበባ፣ በባቱና በተለያዩ ከተሞች የሚካሄዱ የጥምቀት በዓላት ላይ ለመታደም የሚመጡ ቱሪስቶች የኢትዮጵያ የበዓል አከባበር፣ የእርስ በእርስ ግንኙነቱ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን እንዲሁም በተጓዳኝ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችንም ለመመልከት አቅደው እንደሚመጡ ገልጸዋል።

በመሆኑም በየአካባቢው የሚገኙ አስጎብኚዎችና የተለያዩ ዜጎች መልካም ስብዕና በተላበሰ መንገድ ስለአገራቸው በጎውን ይበልጥ ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ጥምቀት ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፉ የተሻለ ገቢ እንድታገኝ የሚረዳ የአደባባይ በዓል ነው። በመሆኑም ለበዓሉ የሚመጡ ቱሪስቶችን በአግባቡ ተቀብሎ በማስተናገድ ረገድ ሁሉም የበኩሉን ሚና ሊወጣ እንደሚገባ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የጥምቀት በዓል የዳያስፖራው ማኅበረሰብ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች ከተለያዩ አገራት በመምጣት የሚታደሙበት በዓል በመሆኑ የሚመጣው ቱሪስት ወደአገሩ ሲመለስ ስለኢትዮጵያ መልካም ገጽታ እንዲያስተዋውቅ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

የበዓሉ ታዳሚዎችም በየአካባቢያቸው በሥነምግባር የታገዙና አንድነትን የሚያጠናክሩ ሥርዓቶችን በመከተል መንገድ ኢትዮጵያዊ ጨዋነታቸውን እንዲያሳዩ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በዓሉ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች በማደራጀት በየአካባቢዎቻቸው ተገቢውን ሥራ እንዲያከናውኑ የሚረዳ ዝግጅት መጠናቀቁንም ተናግረዋል።

በዓሉ በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ የጸጥታ አካላት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ወጣቶች፣ የሚዲያ አካላት እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማገዝና ለሰላም ዘብ በመቆም የበኩላቸውን እንዲወጡ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# «የተገኘውን ሰላም አብዝተን ልንጠብቀውና ዘላቂ ልናደርገው ይገባል»

- ሀጂ አወል አርባ

በዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- የተገኘውን ሰላም አብዝተን ልንጠብቀውና ዘላቂ ልናደርገው ይገባል ሲሉ የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሀጂ አወል አርባ ተናገሩ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አሻራ መጽሐፍ በአፋርኛ ቋንቋ በማዘጋጀቱም ምስጋና አቅርበዋል።

ሀጂ አወል አርባ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዘጋጅነት «ሰላም፣ አንድነት፣ ልዕልና ለኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በአፋር ክልል ሰመራ ላይ በተካሄደው 13ተኛው «ስለ ኢትዮጵያ» አውደርዕይና የፓናል ውይይት ላይ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለፁት፤ የተገኘውን ሰላም አብዝቶ መጠበቅና ዘላቂ ማድረግ ይገባል።

የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን እየፈታን ለሰላም ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮችን እየመነጠርን አገራዊ አንድነትን ልናስጠብቅ ይገባል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ አሁን የተገኘውን ሰላም አብዝተን ልንጠብቀውና ዘላቂ ልናደርገው ይገባል ብለዋል።

ሰላም የሕግ የበላይነት፣ ፍትህ እና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ጉዳይ መሆኑን በመናገርም፤ በቀጣይም የተገኘውን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ አንድ የሆነ ጠንካራ የሥራ ባህል ያለው ሕዝብ እንደሚያስፈልግ እና ተቋማዊ አቅም ግንባታ ላይ ትልቅ ሥራ እንደሚጠበቅ ነው ያብራሩት።

ግጭቶችን በንግግር መፍታት ትልቅ ቁምነገር መሆኑን የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በመሣሪያ አፈሙዝ አሸናፊ ከመሆን በውይይት ማሸነፍ ይበልጣልና ችግርን በውይይት የመፍታትን ጥበብ ማዳበር እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል።

ጀግና መሪ ማለት አገርንና ሕዝብን ከጥፋት የሚያድን ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ጅማሬውን ሳይሆን ፍፃሜን አይቶ አገርን የሚታደግ መሆኑን በመግለፅ አገራዊ አንድነቱ የተጠበቀ ሕዝብ ደግሞ ታላቅ አገር መፍጠር ይችላል ሲሉ ተናግረዋል።

አፋር ጠንካራ የመደማመጥና የመወያየት ባህል አለው ያሉት ሀጂ አወል አርባ፤ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች የአንድነት ጥቅም ኩራት መሆኑን አይተናልም ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተጓዦች መቀሌ ሲገቡ የሕዝቡን ስሜት የተመለከተ ሰው ሰላም ምን ማለት እንደሆነ ይገባዋል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ሰላማዊ በሆነ መንገድ አገራዊ አንድነትን ለማምጣት ጠንካራ ሠራተኛ፣ ሕዝብ እንዲሁም ጠንካራ የጸጥታ ተቋማት ሊኖሩ ይገባልም ብለዋል።

ሀጂ አወል አርባ አሻራ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በአፋርኛ ተዘጋጅቶ በክልሉ በመመረቁም የተሰማቸውን ክብርና ምስጋና በማቅረብ አሻራ መጽሐፍ ለትውልድ የሚተርፍ በጎ አሻራውን እያሳረፈ በመሄድ ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

# በክልሉ በበጋ መስኖ ለማልማት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ፋይዳ አለው። እንዲሁም ከአገር ውስጥ ፍጆታ የተረፈውን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብም የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ያስችላል።

በበጋ መስኖ ልማት ምርታማነትን የሚቀንሱ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ለመስጠት በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ኡስማን፤ በክልሉ ለመስኖ ልማት የሚሆኑ የውኃ ምንጮች ለማስፋት አነስተኛ ጉድጓድ ቆፍረው በሚያለሙ አካባቢዎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የውሃ መሳቢያ ፓምፖች በማዳረስ ረገድ ውጤታማ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰዋል።

ሆኖም የነዳጅ እጥረት በማጋጠሙ አርሶ አደሮቹ የነዳጅ ጥያቄ በማንሣታቸው በየደረጃው ካለው አመራር ጋር በመነጋገር ችግሩን ለመፍታት እየተሠራ እንደሆነ ኃላፊው ጠቁመዋል።

እየተካሄደ ባለው የበጋ መስኖ ልማትም በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ መነቃቃት መፈጠሩን ያነሱት አቶ ኡስማን፤ በበጋ መስኖ ልማትም ወጣቶች፣ ሴቶችና ከስደት የተመለሱ ዜጎች በቡድን በመደራጀት ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን ተናግረዋል።

የበጋ መስኖ ልማቱም ትኩረት ተሰጥቶት በማኅበረሰብ ንቅናቄ እየተመራ በአመራሩና ሙያተኛው ድጋፍ እየተሰጠ የሚያጋጥሙ ችግሮች ወዲያው እየተፈቱና በቁርጠኝነት እየተሠራ እንደሆነ ገልፀዋል።

የበጋ መስኖ ልማት ካስገኛቸው ጠቀሜታዎች አንዱ አርሶ አደሩ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኝና ጊዜውን በአግባቡ ልማት ላይ እንዲያውል ማድረጉን አመልክተዋል።

ከታኅሣሥ እስከ የካቲት ወራት ባለ ጊዜ ውስጥ ምርት የሚሰበሰብበትና ምርቱ ገበያ ላይ የሚሸጥበት ወቅት በመሆኑ ብዙ አርሶአደሮች ምርት በመሸጥ ገንዘብ የሚያባክኑበት ጊዜ እንደሆነ የገለፁት አቶ ኡስማን፤ አሁን ግን ያ ቀርቶ በማሳ እንዲውሉና ገንዘባቸውን ካላስፈላጊ ወጪ እንዲቆጠቡ ምቹ አገጣሚ መፍጠሩን ጠቁመዋል።

የክልሉ የበጋ መስኖ ልማትን ከሁሉም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ወደ ተግባር እንደገባ አቶ ኡስማን አስታውሰዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወንጀልን በመከላከሉ ሥራ የሕዝብ ተሳትፎ በከፍተኛ መጠን ሊያድግ ይገባል!

ሌብነት፣ ዘረፋ፣ ቅሚያ፣ ማጭበርበር እና ሌሎችም በሰው ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተለይ በከተሞች አካባቢ እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ እነዚህ ወንጀሎች በቀንም ሆነ በሌሊት፤ በስውርም ይሁን በአደባባይ፤ በግልም ይሁን በተደራጀ መልኩ ከአነስተኛ ገንዘብ እስከ ከፍተኛ ንብረት ከግለሰቦችም ሆነ ከተቋማት ሲዘረፍ፣ ሲሰረቅ፣ ሲጭበረበርና በቀማኞች እጅ ሲገባ ማየትና መስማቱ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ይህ ተግባር ዛሬ ላይ በርካታ ዜጎችን ለችግር እየዳረገ ብቻ ሳይሆን፤ ወጥቶ በመግባት እንቅስቃሴያቸው ላይ ትልቅ ስጋትም ሆኗል፡፡

ከስርቆት፣ ዘረፋ እና በሌሎችም የማጭበርበር ስልቶች የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተለይ በአዲስ አበባ እና ሌሎችም ትላልቅ ከተሞች አካባቢ እየተበራከቱ መምጣታቸውን ተከትሎ ችግሩን ለመግታት እና ለመከላከል እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በአዲስ አበባ ከመኪና ስርቆት ጀምሮ የግለሰቦችን ኪስና ቦርሳ እስከማውለቅ የሚደርሱ የሌብነት ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ አበረታች ሥራዎች ስለመኖራቸው ፖሊስ ከሚያወጣቸው ሪፖርት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ በፖሊስ እና በሌሎች የመንግሥት የፀጥታና ደህንነት አካላት የሚከናወኑ ተግባራት ብቻቸውን የሚፈለገውን ውጤት የሚያመጡ አለመሆናቸው እሙን ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ወንጀሎች የሚፈጸሙት በተጠናና በታቀደ መልኩ ከመሆኑም በላይ፤ ወንጀል ፈጻሚዎቹ ከኅብረተሰቡ እይታ ውጪ ያልሆኑ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ወንጀሉን ከመከላከል አኳያ ኅብረተሰቡ እነዚህን ሌቦችና ዘራፊዎች በሚመለከትበት ወቅት ለሕግ አካል መጠቆም ወይም እንዲያዙ መተባበር ይኖርበታል፡፡

በዚህ መልኩ የሕዝብ ተሳታፎ በጉልህ የሚገለጽባቸው አካባቢዎች የመኖራቸውን ያህል፣ ችግሩን እያዩ እንዳላዩ የሚያልፉ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችም አሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሌቦቹ፣ ቀማኞዎቹና አጭበርባሪዎቹ ቦታና ሁኔታን እያዩ የወንጀል ተግባራቸውን እንዲፈጽሙ የልብ ልብ የሚሰጣቸው ነው፡፡ ለዚህም ነው ሌብነት የቀነሰባቸው ሰፈርና አካባቢዎች የመኖራቸውን ያህል፤ ሌባ በስፋት የሚፈነጭባቸው ሰፈርና አካባቢዎች መበርከታቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የዚህ የዘረፋ እና ስርቆት መገለጫ ተጨማሪ መስክ ሆኖ የመጣው ሐሰተኛ መታወቂያ በማዘጋጀት የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት አባል ነን የሚል የማጭበርበሪያ አካሄድን የሚጠቀሙ ግለሰቦች መታየታቸው ነው፡፡ ይህ አካሄድ ለሚፈጽሙት ወንጀል ማደናገሪያ እና እንደ ማስፈራሪያም ያገለግላቸው ዘንድ ለዚህ እኩይ ተግባራቸው እንደ መከለያ መጠቀም ያስችላል ብለው ያሰቡትን አንድን የመንግሥት ተቋም መታወቂያ በማዘጋጀት ከተቋም የተላኩ በማስመሰል የሚፈጽሙት ውንብድና ነው፡፡

በዚህ መልኩ ለወንጀል የሚሰማሩ ግለሰቦች በአብዛኛው የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎትን መታወቂያ በሃሰተኛ መልኩ በማዘጋጀት የሚጠቀሙና የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ሰሞኑን ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ሐሰተኛ መታወቂያ በማዘጋጀት የደኅንነትና የሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት አባል ነን የሚሉ ግለሰቦች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ ይሄን አስመልክቶም አገልግሎቱ በተለያዩ መንገዶች ክትትል ሲያደርግ የቆየ ሲሆን፤ በዚህ መልኩ ኅብረተሰቡን እያጭበረበሩ በሚገኙ ግለሰቦች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡

ሰሞኑን በተደረገ ጥብቅ ክትትልም፣ ፈለቀ ዴብሳ ደማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02፣ አስፋው አዳማ ሙታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01፣ ሳምሶን ገነነ መንገሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5፣ ተስፋ ሀተው ገምቴሳ በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ሰበታ ክፍለ ከተማ፣ ዮሰን በቀለ ትከሳ በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ቡራዩ ክፍለ ከተማ ሐሰተኛ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎትን መታወቂያ ይዘው ሲንቀሳቀሱ በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ የሌሎች መንግሥታዊ ተቋማትንም ሐሰተኛ መታወቂያ በመጠቀም ለሕገወጥ ድርጊት የሚያውሉ ግለሰቦችም በጸጥታ አካላት የተቀናጀ ሥምሪት ተይዘዋል፡፡

እነዚህን አጭበርባሪዎች ተከታልሎ በመያዝ እና በሕግ እንዲጠየቁ በማድረግ በኩል በመንግሥት በኩል እየተደረገ ያለው ጥረት እና እየተወሰደ ያለው ርምጃ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ጥረት ብቻውን ለውጤት የሚበቃ ባለመሆኑ እነዚህን አጭበርባሪዎች ተከታትሎ ለሕግ አካል የማሳወቅና የመንግሥት አጋዥ አቅም መሆን ከኅብረተሰቡ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ ኅብረተሰቡ የመንግሥታዊ ተቋማት አባል ነን በማለት በሐሰተኛ መታወቂያ የማጭበርበር ድርጊት ለመፈጸም ከሚሞክሩ ግለሰቦች ጋር በተያያዘ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ለጥቆማ በተዘጋጁ መስመሮች ጭምር ለብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት፣ ለኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ፣ እንዲሁም በየደረጃው ላሉ የፀጥታ አካላት ጥቆማ በማድረስ በተለይም በከተሞች አካባቢ እየተበራከቱ የመጡ ወንጀሎችን በጋራ መከላከል ይገባል!


እፎይ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

# ሊፈተሹ የሚገባቸው የህገ ወጥ ስደት ምክንያቶች

**መሳኩ ሔርሴ**

ኢትዮጵያውያን ለስደት ከሚወጡባቸው አገራት አንዷ ወደሆነችው ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚያደርጉት ጉዞ እጅግ አደገኛ ከሚባሉ ስደት ኮሪደሮች መካከል ተጠቃሽ ነው።ደቡብ አፍሪካ ለመግባት የስድስት ሀገራትን ድንበር መሻገር ይጠበቅባቸዋል።ደቡብ አፍሪካ ከኢትዮጵያ በስተደቡብ 4 ሺህ 777 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን ይህ የስደት ኮሪደር በዓለም ውስጥ ከሚገኙ ረጅም የስደት ኮሪደሮች መካከል አንዱ ተደርጎ ይጠቀሳል፡፡

ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ስደት የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚደረግ ሲሆን፤ የአየር ትራንስፖርት፣ የውሃ ላይ ትራንስፖርት፣ እና የየብስ ትራንስፖርትን በመጠቀም በርካታ የአፍሪካ ሀገራትን በማቋረጥ የሚደረግ ነው።አንዳንዶቹ ከአዲስ አበባ ወደ ጆሃንስበርግ ቀጥታ በረራ የሚያደርጉ ሲሆን፤ አብዛኛው ስደተኛ ግን የአውቶብስ ትራንስፖርት እና የእግር ጉዞንን በማጣመር የመተላለፊያ አገሮችን ያቋርጣሉ። አንዳንዶች ደግሞ በህንድ ውቅያኖስ ላይ በጀልባ ይጓዛሉ።

በተለምዶ ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው የየብስ ትራንስፖርት ከኬንያ የሚጀምር ሲሆን፤ ከዚያም በታንዛኒያ፣ በማላዊ፣ በሞዛምቢክ/ዚምባብዌ ወደ ደቡብ አፍሪካ ይዘልቃል። ዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት እ.አ.አ በ2021 ባወጣው ሪፖርት ከ2016 እስከ 2018 ድረስ ብቻ ወደ ደቡብ አፍሪካ የገቡ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ቁጥር ከ200 ሺህ እስከ 300 ሺህ ይገመታል፡፡

ይህ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ረጅም የስደት ጉዞ በአደጋዎች የተሞላ ነው። በመሸጋገሪያ አገሮች ውስጥ ብዙ ስደተኞች እንደወጡ ቀርተዋል። ዓለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት ባካሄደው ጥናት መሰረት እ.አ.አ ከ2012 እስከ 2020 ድረስ ባሉት ስምንት ዓመታት ውስጥ ቅርብ ጊዜ ከሰባት ሺህ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ከኢትዮጵያ ተነስተው ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመሄድ ከቤታቸው ወጥተው የደረሱበት አይታወቅም ወይም ሞተዋል፡፡

በዚህ መልኩ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገው ጉዞ በተግዳሮቶች የተከበበ እና ለአደጋ የሚያጋልጥ ቢሆንም፤ በደቡብ አፍሪካ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ የኢትዮጵያውያን ስደተኞች አሉ። ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ገንዘብ በመላክ በሀገር ቤት የሚኖር ቤተሰባቸውን የሚደግፉ ሲሆን፤ በሀገራቸው የሚያፈሱት የኢንቨስትመንት መጠንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው።አንዳንዶቹም እምነት ተቋማትን ጭምር ለመደገፍ ገንዘብ ይልካሉ።በተጨማሪም በትውልድ ቦታቸው የሚገኙ አካባቢያዊ እና ብሄራዊ የልማት ፕሮጀክቶችን በገንዘብ ይደግፋሉ፡፡

እናም በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለሀገር ኢኮኖሚ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም። በተለያየ መልኩ ተሰድደው በተለያዩ አገራት ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ኢትዮጵያ በዓመት ከአምስት ቢሊየን ዶላሮች በሪሚተንስ ታገኛለች።በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንም ኢትዮጵያ ለምታገኘው ሪሚታንስ የራሳቸውን ድርሻ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ከመላው ሀገሪቱ የሄዱ ቢሆኑም፤ አብዛኞቹ ግን ከሀዲያ ዞን እና ከከምባታ ጠምባሮ ዞን የሄዱ ናቸው። የሀዲያ ዞን የሰው ሀብት እና ማህበራዊ ጉዳዮች መምሪያን ጠቅሶ፣ ደረጀ ፈይሳ የተሰኘ ተመራማሪ በጥናታዊ ጽሁፉ ላይ እንዳስቀመጠው፤ እ.አ.አ ከ2013 እስከ 2018 ባሉት አምስት ዓመታት 61 ሺህ 148 ወጣቶች ወደ ደቡብ አፍሪካ ተሰደዋል።ይሄው ተመራማሪ ባካሄደው የዳሰሳ ጥናት መሰረት ከሀዲያ እና ከከምባታ ጠምባሮ ዞኖች ውስጥ ከሚኖሩ ቤተሰቦች ውስጥ 40 ከመቶ የሚጠጋ ቤተሰብ ቢያንስ አንድ ዓለም አቀፍ ስደተኛ አለው።

ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሚደረገው ስደት ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የአንበሳውን ድርሻ ይይዛል።በእርሻ መሬት ላይ ያለው ጫና መጨመር ደግሞ ከሀዲያ እና ከምባታ አካባቢዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሚደረገው ስደት ቁልፍ ከሆኑ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች አንዱ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት ካለባቸው የሀገራችን አካባቢዎች አንዱ ነው።በካሬ ኪሎ ሜትር 342 ነጥብ 64 ሰው ይኖራል። ሀገራዊ የህዝብ ጥግግት በካሬ ኪሎ ሜትር 109 ነጥብ 22 አንጻር ሲታይ እጅግ የላቀ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።ይህ የህዝብ ጥግግት በእርሻ መሬት ላይ የበለጠ ጫና ፈጥሯል።ምርታማነት እያሽቆለቆለ እንዲሄድም ምክንያት ሆኗል፡፡

የአቶ ደረጀ ጥናት እንደሚያሳየው የሀዲያ አካባቢ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በሚከሰተው ድርቅ በተደጋጋሚ ከሚጠቁ አካባቢዎች አንዱ ነው።ይህም የግብርና ስራ ላይ አደጋ ፈጥሯል።ይሁን እንጂ እነዚህ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በሀዲያ ዞን ብቻ ያሉ ችግሮች አይደሉም።ችግሮቹ ሀዲያ ከጎረቤቶቹ ጋር የሚጋራቸው ናቸው።በአካባቢው ያሉ አንዳንዶቹ ዞኖች እንዲያውም ከሀዲያ ከፍ ያለ የህዝብ ጥግግት አላቸው። ይሄም "ታዲያ ከሀዲያ አካባቢ እንዴት ከፍተኛ ስደተኛ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሊሰደድ ቻለ?" የሚል ጥያቄ የሚያጭር ይሆናል፡፡

አንዳንድ ሰዎች የሀዲያ አካባቢ ወደ ደቡብ አፍሪካ እየተሰደዱ ያሉት ለመሰደድ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ አቅም ስላላቸው ነው የሚል መከራከሪያ ሲያቀርቡ ይታያል።ሆኖም ይሄ እጅግ የተሳሳተ መከራከሪያ ነው። የሀዲያ ወጣት ወደ ደቡብ አፍሪካ እየተሰደደ ያለው ለመሰደድ የሚያስችል የኢኮኖሚ አቅም ስላለው አይደለም።የኢኮኖሚ አቅም ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ከጎረቤት ዞኖች ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚሰደዱ በርካታ ስደተኞችን እናይ ነበር። አጎራባች ዞኖች የሚኖሩ ህዝቦች ከሀዲያ ያነሰ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው አይደሉም።አንዳንዶቹ ከሀዲያ አካባቢ የተሻለ የኢኮኖሚ አቅም ያደረጁ ናቸው፡፡

ከሀዲያ እና ከምባታ ዞኖች አካባቢ የሚደረገውን ስደት ለማብራራት ከኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ባሻገር ያሉ ምክንያቶችን ማብራራት አስፈላጊ ነው።ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ምክንያቶች በተለይም "የዳርፍሪማ" የሚባለው የማህበረሰቡ እሳቤ፣ ለስደት የሚሰጠው መንፈሳዊ ትርጉም፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ኔትወርክ እየተጫወቱ ያለውን ሚና መመርመር አስፈላጊ ነው።ምክንያቱም እነዚህ ለስደት የበኩላቸውን እየተወጡ ቢሆንም፤ ምሁራን በጥናታቸው፣ መንግስትም በመከላከል ትኩረቱ ውስጥ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጣቸው በመሆናቸው ነው፡፡

ቀደም ብዬ ባነሳሁት የአቶ ደረጀ ጥናት፣ በተለይም ከሀዲያ አካባቢ የሚደረገው ስደት እንቅስቃሴ በእጦት ምክንያት ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ማህበረሰብ ስደትን እንደ መብት ይመለከተዋል።የተሻለ እድል ወዳለበት አካባቢ ሄዶ መስራትን እና መለወጥ በአካባቢው እንደ ባህል ሆኗል።ቀደም ባሉ ጊዜያት በሀገር ውስጥ የተሻለ እድል ወዳለባቸው አካባቢዎች ሄዶ የመስራት ባህል የነበረው ህዝብ ሲሆን፤ ይሄ የተሻለ እድል ወዳለበት ሄዶ መስራት በሀዲይሳ "ዳርፍሪማ" ይሰኛል።ጋምቤላ፣ ወንጂ እና ድሬዳዋ አካባቢ የሀዲያ ማህበረሰብ በብዛት መኖሩ በአካባቢው ስር የሰደደ የዳርፍሪማ ባህል እንዳለው ማሳያ ነው።ከዚህ በተጓዳኝ መንፈሳዊ እይታው ሲሆን፤ ለምሳሌ፣ አንድ ስደተኛ በመንገድ ላይ የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች ተሻግሮ ካሰበበት ቦታ ሲደርስ እና ተሳክቶለትም ከተገኘ፣ ቀድሞውኑ ፈጣሪ ያዘዘለት እድል እንደሆነ ይነገርለታል፤ በአንጻሩ ካሰበበት ሳይደርስ ቢቀር የፈጣሪ ፈቃድ ስላልሆነ ነው የሚል እሳቤ በመያዙ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ጥናት ባለቤት አቶ ደረጀ እንደሚሉትም፤ ከኢኮኖሚያዊ አቅሙ ባሻገር ፖለቲካዊ ኔት ወርክ እና ማህበራዊ ኔት ወርክ የበኩሉን ሚና ሲጫወት ቆይቷል።ቀደም ባሉ ጊዜያት የመንግስት ባለስልጣናት ስደትን ማበረታታቸው እና በኢትዮጵያ ደቡብ አፍሪካ ኮሪደር የሚንቀሳቀሱ ደላሎች ጋር የመገናኘት እድል በራሱ በአካባቢው ለስደት ምክንያት ነው።በመሆኑም ዛሬ ላይ ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረገውን ስደት ለማስቆም በሚደረገው ጥረት ከኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ባሻገር የቆየውን ስደት ባህል፣ የመንፈሳዊ ፈቃድ እሳቤ እንዲሁም ፖለቲካዊና ማህበራዊ ኔትወርኮችን ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ጋዜጠኛዋ የፋሽን ዲዛይነር

**አስናቀ ፀጋዬ**

በሸማ ጥበብ ተመርተው ለገበያ የሚቀርቡ ባህላዊ አልባሳት በአይነት፣ በጥራት፣ በዲዛይንና በቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መጥተዋል። የአልባሳቱ ተጠቃሚዎችም ኢትዮጵያውን ብቻ ሳይሆን የውጭ ሀገራት ዜጎችም ሆነዋል። ታዲያ እነዚህ ባህላዊ አልባሳት በብዛት በሸማቹ ዘንድ ጥቅም ላይ የሚውሉት የበዓል ወቅትን ተከትለው ነው። በተለይ በክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዘንድ የባህል አልበሳቱ ገና፣ ጥምቀት፣ ፋሲካና አዲስ ዓመት በዓላት ሲመጡ ገበያቸው ይደራል። ተፈላጊነታቸውም ይጨምራል። ከበዓላት ውጭ አልባሳቱ ለሰርግ፣ ልደትና ለሌሎችም ሃይማኖታዊ ፕሮግራሞች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

ከበዓላትና ከሌሎች ፕሮግራሞች በተጨማሪ ግን አልባሳቱ በስራ ቀናት ሰዎች ሲለብሷቸው አይታዩም። ልብሶቹ ነጭና ቆሻሻ የማይችሉ በመሆናቸውና ይህንንም ተከትሎ በስራ ቦታ ብዙም ምቾት የማይሰጡ ስለሆኑ በሰዎች ዘንድ ተመራጭ እንዳልሆኑም ይነገራል። አሁን አሁን ግን የባህል አላባሳቱ ከሌሎች ዘመናዊ አልባሳት ጋር ተዋህደው በስራ ቀናትም ጭምር ሰዎች እንዲለብሷቸው በተለየ ዲዛይን ልብሶቹን አዘጋጅተው ለገበያ የሚያቀርቡ አልጠፉም።

ከነዚህ ውስጥ አንዷ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋዜጠኛዋ ቤቴልሔም ጥጋቡ ናት። ቤቴልሔም ጥጋቡ ከጋዜጠኝነት ስራዋ ጎን ለጎን ባህላዊ አልባሳትን በዘመናዊ መንገድና ከመደበኛ የስራ ልብሶች ጋር ተዋህደው እንዲለበሱ በተለየ ዲዛይን በቤቷ በማዘጋጀት ለገበያ ታቀርባለች።

ጋዜጠኛዋ የባህላዊ አልባሳቶቹን በተለየ ዲዛይን አዘጋጅታ ሰዎች ከበዓላት ወቅት ውጭ በአዘቦት ቀንም ጭምር ከሌሎች ልብሶች ጋር አቀላቅለው እንዲልብሱ የማድረጉን ስራ የጀመረችው በቤቷ ሲሆን በቅድሚያ ስራዎቿን እንካችሁ ያለችው ለስራ ባልደረቦቿ ነበር። የስራ ባልደረቦቿም አላሳፈሯትም። በስራዋ ተደንቀው በሚፈልጉት ትእዛዝ በልዩ ዲዛይን ያዘጋጀችላቸውን





አልባሳት ገዝተው ለብሰዋል። ከራሳቸው አልፈው ሌሎችም በእርሷ የተዘጋጁትን የባህል አልበሳት እንዲለብሱ አድርገውላታል።

በዚህ የተጀመረው የጋዜጠኛዋ የባህል አልባሳትን በተለየ ዲዛይን አዘጋጅቶ ለገበያ የማቅረብ ሥራ ዛሬ ላይ ተጨማሪ ገበያ እየሳበላት የመጣ ይመስላል። ምርቶቿም በተጠቃሚዎች ዘንድ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ መጥቷል። ‹‹መቀነት የልብስ ንድፍ›› በሚል ስያሜም በህፃናት፣ በልጆችና በአዋቂዎች ከበዓላት ውጭ በሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በየትኛውም ጊዜ ከሌሎች ዘመናዊ ልብሶች ጋር ተቀላቅለው ሊለበሱ የሚችሉ አልባሳትን ለተጠቃሚዎች እያቀረበች ነው። ከዚሁ ጎን ለጎንም በክር የህፃናት ጫማዎችንና የግድግዳ ጌጣጌጦችንም በእጇ ሰርታ ከስራ ባልደረቦቿ ባሻገር የሌሎችንም ቀልብ ስባለች።

በአሁኑ ጊዜ ባህላዊ አልባሳትን በተለየ ዲዛይን በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቡ ዲዛይነሮች ቁጥር ጥቂት የማይባል ባይሆንም ጋዜጠኛ ቤቴልሔም እነዚሁ አልባሳትን በዘመናዊ መንገድና በተለየ ዲዛይን በማዘጋጀት ከበዓላት ውጭ በስራ ቀንም ጭምር በክርስትና እምነት ተከታዮች ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ተወዳጅና ተፈላጊ ሆነው እንዲለበሱ በማድረጓ ስራዎቿን ከሌሎቹ ለየት ያደርገዋል። ሲለበሱ ቀለል ያሉና ምቾት የሚሰጡ መሆናቸውም በተጠቃሚዎች ዘንድ ይበልጥ ተመራጭ ያደርጋቸዋል።

በተጨማሪም የምታዘጋጃቸው አልባሳት በየትኛውም የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች በፈለጉት ቦታ ሊለብሷቸው የሚችሉ ናቸው። የጋዜጠኛዋ ዋናው እሳቤም አልባሳቱ በተለየ ዲዛይን ተሰርተው ከክርስትና እምነት ተከታዮች በዘለለ የሌሎች እምነት ተከታዮችም ጭምር በስራም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ላይ እንዲለብሷቸው ማድረግ ነው። በበዓላት ወቅት ብቻ የሚለበሱትን የባህል አልባሳት በተለየ ዲዛይን በማዘጋጀት በአዘቦት ቀንም እንዲለበሱ የማድረግ ትልምም ይዛ ነው የተነሳቸው።

እነዚህ የባህል አልባሳት በተለያየ መጠን ከህፃናት እስከ አዋቂዎች ድረስ በአብዛኛው በትእዛዝ የሚዘጋጁ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ጋዜጠኛዋ የተለየ የዲዛይን ሃሳብ ከመጣላት ልብሱን አዘጋጅታ ለገበያ ታቀርባለች። የልብሶቹም ዋጋ ብዙም ኪስ የማይጎዳ ሲሆን ልብሱ የሚሰራበት ቁሳቁስ ከግምት ውስጥ ገብቶ ለአዋቂዎች ከ700 እስከ 1200 ብር ይሸጣል። ለህፃናትና የልጆችም በዚሁ ዋጋ መካከል ሆኖ ለገበያ ይቀርባል።

ደምበኞቿ ጋር የምትደርሰው ‹‹መቀነት የልብስ ንድፍ›› በሚለው የቴሌግራም ገፅ ሲሆን ደምበኞች በዚሁ ገፅ ገብተው በተለጠፈው ስልክ ቁጥር በመደወል በሚፈልጉት ዲዛይን እንድታዘጋጅላቸው ያደርጋሉ። በተጨማሪም ደምበኞች በባህል ጨርቅ የተሰሩ ጋወን፤ ለቀሚስ ለሱሪ አላባሽ ፤ የክር የሳሎን ጫማዎችን፤ ስካርፎችን፤ ቦርሳዎችን እዚሁ ገጽ ላይ ማግኘት እና ማዘዝ ይችላሉ። ከዚህ ውጭ አብረዋት የሚሰሩ የስራ ባልደረቦቿም ምርቶቿን በመግዛት ያበረታቷታል፤ ሌሎችም እንዲገዙላት ያስተዋውቁላታል። በዚህም የምርቱ ፈላጊ ደምበኞች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል።

የኢትዮጵያ ባህላዊ አልባሳት ከሀገር ውስጥ ባለፈ በውጭ ዜጎችም ጭምር ይፈለጋል። ነገር ግን አልበሳቱን በተለየ ዲዛይንና የሁሉንም ፍላጎት ባማከለ መልኩ መስራት ላይ ገና ብዙ ይቀራል። እንደ ጋዜጠኛ ቤቴልሔም ጥጋቡን የመሰሉና ባህላዊ አልበሳቱን በተለየ ዲዛይንና ለሁሉም በሚስማማ መልኩ በማዘጋጀት ለገበያ የማቅረቡ ጅምር ግን ይበል የሚያሰኝ ነው። ይህ ጅምር ባህላዊ አልባሳቱ ከሀገር ውስጥ ባለፈ በውጭ ሀገራት ያሉ ዜጎችንም ጭምር ቀልብ በመሳብ የውጭ ምንዛሬን የሚያስገኝ ነውና ጅምሩ በሌሎችም ዲዛይነሮች ሊጠናከር ይገባል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ጥበብ የገሃዱን ዓለም እውነታ ሁሉ ማንጸባረቅ አለበት?

**ቦጋለ አበበ**

የጥበብ ዋነኛውና ትልቁ አላማ የአንድን ማህበረሰብ መልካም እሴት መገንባት ነው። የነበረና የኖረን የማህበረሰብ መልካም እሴት እንዳይናድና ወደ መጥፎ አቅጣጫ እንዳያመራ መጠበቅም የጥበብ አንዱ ኃይል ነው። ያው ጥበብ ሲባል አንዱና ዋነኛው ሙዚቃ ነውና በኢትዮጵያ ሙዚቃዎች ውስጥ ከዚህ አኳያ የሚስተዋሉ የሀሳብ ተቃርኖዎች አስገራሚ ናቸው።

ለዚህ እንደመነሻ እንዲሆን ለዛሬ ብዙዎችን የሚያከራክር አንድ ሀሳብ እናንሳ። በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ በታላላቅና አንጋፋ ሙዚቀኞች ጭምር የተዜሙ ራስ ወዳድነትን ወይም ከምንም በላይ ለገንዘብ ዋጋ መስጠትን የሚሰብኩ ዘፈኖች ጥቂት አይደሉም። እነዚህ ዘፈኖች በብዙ ሰዎች ዘንድ እጅግ ተወዳጅና ሙዚቃዎቹን ያዜሙትም አርቲስቶች ልዩ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው። ለምሳሌ ያህል በዚሁ ሀሳብ ዙሪያ በተወዳጅ አርቲስቶች የተዜሙ ተወዳጅ ዘፈኖች የመልእክታቸውን ጭብጥ በጥቂቱ እንመልከት:-

“እያለህ ካልሆነ ከሌለህ የለህም” ክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ፣

“ኪስህ ነው የቅርብ ወዳጅህ” ኤፍሬም ታምሩ፣

“ አብሮ መብላት ተሳስቦ ኑሮ ገዳም ሰፈር ቀረ ድሮ” አብዱ ኪያር፣

ተመሳሳይ መልእክትና ጭብጥ ያላቸው ሙዚቃዎቻችን እነዚህ ብቻ አይደሉም። ትዝብቴ ሙዚቃዎቹ ላይ ትችት መሰንዘር ሳይሆን ሙዚቃዎቹ የሚያስተላልፉት መልእክት ላይ በመሆኑ እነዚህን ዝነኛና ተወዳጅ ዘፈኖች ለአብነት ከጠቀስኩ በቂ ነውና ወደ ዋናው ሃሳብ ልለፍ።

እውነት ለመናገር እንደዚህ አይነት ጭብጥ ያላቸው ሙዚቃዎች መረዳዳት የኢትዮጵያውያን ባህል ነው በሚባልበት ማህበረሰብ ውስጥ መልካም የተባለውን እሴት የሚቃረኑ ናቸው። ከዚያም በላይ እንደዚህ አይነት መልእክቶችን ያዘሉ ሙዚቃዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የካፒታሊዝም አስተሳሰብን የሚሰብኩ ናቸው ማለት ይቻላል። እርግጥ ነው የእነዚህ ዘፈኖች ጭብጥ በገሃዱ ዓለም ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በትክክል የሚገልጽ ሊሆን ይችላል። ጥበብ ደግሞ የገሃዱ ዓለም ነጸብራቅ ነው የሚል ክርክርም ከዚህ አኳያ ሊያስነሳ ይችላል። ጥያቄው ግን ጥበብ የገሃዱ ዓለም ነጸብራቅ ቢሆንም ሁሉንም የገሃዱ ዓለም እውነታዎች ገሃድ ማውጣት ወይም “ፕሮሞት” ማድረግ አለበት ወይ ነው?። እዚህ ጋር ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር የተያያዘ አንድ ምሳሌ የበለጠ ይህን ሃሳብ ሊያብራራ ይችላል። በጋዜጠኝነት ሙያ ውስጥ ዜና የሆነ ነገር ሁሉ አይዘገብም፣ የሙያ ስነምግባር የሚባል ነገር አለ፣ አንድ ጋዜጠኛ የሆነ ትልቅ ዜና መሆን የሚችል ክስተት ቢገጥመው ከመዘገቡ አስቀድሞ በህዝብ ዘንድ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽእኖ መኖር አለመኖሩን ማሰብ አለበት። ዜናው ምንም ያህል ትልቅ ቢሆን ህዝብ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ ካለ ሊሰራው አይገባም ተብሎ ይታመናል። ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ከሆነ ይተወዋል ማለት ነው። ጥበብም ተመሳሳይ ባህሪ አለው፣ ምንም ያህል የገሃዱ ዓለም ፈጦ የወጣ እውነት ቢኖር ጥበብ እሱን ከማራገብ መቆጠብ እንጂ ማስተዋወቅ አይገባትም። አንድ የገሃዱ ዓለምን እውነታ ጥበብ በይፋ አደባባይ ላይ ባታወጣውም ቀድሞውንም ህዝብ የሚያውቀውና ጸሃይ የሞቀው ሊሆን ይችላል ብለን እናስብ ይሆናል። ነገር ግን አንድ እውነት በጥበብና ጥበበኞች ሲገለጽ የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀድሞም ዓለም ያወቀው ቢሆን እንኳን ቀላል አይደለም። ጥበብ የህዝብ መሪ ናት፣ የጥበበኞችን ሃሳብም ህዝብ ገዝቶት የመከተል እድሉ በጣም ሰፊ ነው። ከዚህ አንጻር ጥበብ የገሃዱን ዓለም እውነታ እያየች እንዳላየች ሆና ትለፍ ሳይሆን አካሄዷን መምረጥ አለባት የሚለው ሃሳብ የበለጠ ገዢ ይሆናል።

ይህን የምንለው ያለምክንያት አይደለም። ዘፈኖቹ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ስላለ ነው። እስኪ ልብ ብላችሁ አስተውሉ! አንዳንድ ሰዎች ግደለሽ ወይም ብኩን መሆን ሲፈልጉ የአንዱን ዘፈን ይጠቅሱና ‹‹... አለ እገሌ›› ይላሉ። ይሄ ማለት ዘፋኙ ያለውን ነገር ለማድረግ አስበዋል ማለት ነው። ‹‹ስለነገ ምንም አታስብ›› የሚል ይዘት ያለው መልዕክት የሚያስተላልፉ ዘፈኖች አሉ። ይህን የሚሰማ ወጣት ግደለሽ ለመሆን ይበረታታል ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ከነገ የሕይወት መርህ ጋር ይጣረሳል። የሰው ልጅ ትውልድን የሚያስቀጥል ስለነገ በማሰብ ነው።

በምሳሌነት የተጠቀሱት ሙዚቃዎች ዜማና ግጥማቸው ግሩም ነው። ከሚያስተላልፍለት ጭብጥ ሃሳብ አንጻር አንዳንዶቹ የተሻሉ ሆነውም እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ ያህል የክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን “ከሌለህ የለህም” የተሰኘ ሙዚቃ አጠቃላይ ጭብጥ ስንመለከት ለሌሎች አታስብ፣ ከሰው ይልቅ ለገንዘብ ብቻ ተጨነቅ የሚል አጠቃላይ መልእክት የለውም። እንዲያውም ይኑርህ ነው የሚለን። ይህ ደግሞ ክፋት የለውም፣ ማንኛውም ሰው ይኖረውና ሀብት ንብረት ያፈራ ዘንድ የሚቃወም አለ ተብሎ አይታሰብም። የዘፈኑ አጠቃላይ መንፈስ ግን ሰው ሁሉ ጥሪት እንዲኖረው እንጂ ኖሮት የሌላቸውን እንዲረዳና እንዲደግፍ የሚያነሳሳ አይደለም። ከዚያም በላይ ከሌለህ የለህም የሚለው አሻሚ ትርጉም ሰፊው ህዝብ ሁሉ ኖሮት ነው እንዴ የሚኖረው? ወደሚል ጥያቄ ይገፉናል።

ሌላው የኤፍሬም ታምሩ “ኪስህ ነው የቅርብ ወዳጅህ” የሚል ዜማ አጠቃላይ ጭብጥ ለጉምቱው የግጥምና ዜማ ደራሲ ይልማ ገብረአብ ከፍ ያለ አክብሮት ቢኖረኝም በዚህ ሃሳቡ ግን እንዳልስማማ አድርጎኛል። ገንዘብ የቱንም ያህል ቢከመር በርካቶችን ከሞት ማዳን እንደማይችል በብዙ አጋጣሚዎች ታዝበናል። ከዚያ ይልቅ ሰው የሰው የቅርብ ወዳጅ ሲሆን ከብዙ ነገሮች የሰውን ሕይወት ሲታደግ ሁሌም እያስተዋልን ነው። ሰው ኪሱ ሞልቶ ነገር ግን ሰው ርቦት ሲሰቃይ በአንጻሩ ሰው ሰውን ከገንዘብ በላይ ሲያድን ብዙ ምሳሌዎችን ማንሳት ይቻላል። ሰው ከምንም በላይ ወዳጁ ኪሱ ቢሆን ኖሮ ዛሬ መቄዶንያን የመሳሰሉ የረድኤት ድርጅቶች ባልተፈጠሩ ነበር።

በተወዳጁ ድምጻዊ አብዱ ኪያር የተዜመው “አራዳ” የተሰኘ ተወዳጅ ዘፈንም ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ምሳሌዎች የባሰ እንጂ የተሻለ መልእክት የሚያስተላልፍ አይደለም። “አብሮ መብላት ቀረ ድሮ”፣ በኪስህ ተማመን ጎበዝ ፍቅር ጠፍቷል” የሚሉ ስንኞች የዚህ ሙዚቃ ጭብጥ ሃሳቦች ናቸው። ትክክል ነው ሃሳቡ የገሃዱ ዓለም እውነታ ነው። ነገር ግን ፍቅርና መተሳሰብ ጠፍቷል ወይም እየጠፋ ነውና ሰው ሁሉ ግለኝነትን እንዲከተል ከማነሳሳት ይልቅ ለምን መተሳሰብና ፍቅር ይጠፋል? የሚል ጭብጥ የዘፈኖቹ ዋነኛ መልእክት ቢሆን ማህበረሰብን በመልካም እሴት ከመገንባት አኳያ የተሻለ ጥቅም ይኖረዋል። መቼም መተሳሰብና ፍቅር መጥፋቱ ጥሩ ነገር ሊሆን አይችልም፣ ስለዚህ ጥበብ ወደ ጠፋው መልካም እሴት ማህበረሰቡን የመመለስ ሚና ሊኖረው ይገባል እንጂ ከጠፋው ጋር አብሮ መጥፋትን የሚሰብክ አይነት መልእክት(negative energy) መፍጠር የለበትም።

እዚህ ላይ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች የሚሉትን አንድ ነገር እንጥቀስ። ደረጃ እና ተፈላጊነት (Standardization and Popularization) የሚባል ነገር አለ። ደረጃ (Standard) የሚባለው ከያኒው የመጣለትን ነገር እንደ ወረደ ሲያቀርበው ነው። ትክክለኛ የተሰማው ስሜት ሳይጨመር ሳይቀነስ የሚቀርብ ማለት ነው። ሥራው ይወደድም አይወደድም ከያኒው የሚያቀርበው የውስጡ ስሜት ያዘዘውን ነው።

ተፈላጊ (Popular) የሚባለው ደግሞ፤ ማህበረሰቡ ምን ያስፈልገዋል? ምን ቢቀርብለት ነው የሚወድ? የሚለውን ታሳቢ በማድረግ የሚሰራ ነው። ይህም የሚሰራው በመልዕክቱ ትውልድ ለመቅረጽና ለማነጽ ነው።

በኢትዮጵያ ደረጃ የትኛው ነው የሚያስፈልገን የሚለውን ማሰብ ነው። በሬዲዮና ቴሌቭዥን የሚታይና የሚሰማ ነገር ሁሉ ትክክለኛ ነው ብሎ በሚያምን ማህበረሰብ ውስጥ ሊገነባ የሚችል ነገር ነው መተላለፍ ያለበት። ምክንያቱም ገና ማህበረሰብ የማስተማር ደረጃ ላይ ነን። ለዚህ ደግሞ ኪነ ጥበብ ኃላፊነት አለበት!

# ነፃ ሃሳብ

# የሰላም ሀሳብ አዋጥተን የሀገራችንን ሰላም እናጽና

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ለዛሬው መጣጥፌ መር መክፈቻ ይሆነኝ ዘንድ "ኢትዮጵያ ምን አጣች?" ስል በጥያቄ ጀምሬአለሁ። ይሄ ጥያቄ ደግሞ የጋራ ጥያቄችን ነው፤ የምንመልሰውም በጋራ ነው። ሆኖም እኔ የራሴን ምልከታ፤ የግሌን እይታ በሁላችንም ውስጥ ይኖራል ባልኩት ልክ ላነሳ ወደድኩ። እርግጥ ያጣነው ምንም የለም ተፈጥሮ ሙሉ አድርጋ ነው የፈጠረችን። እኛ ግን አንድ ነገር ግን ይጎለናል። እርሱም ተነጋግሮ መግባባት ነው። ተነጋግሮ ባለመግባባት ብዙ ነገሮቻችንን አጥተናል። የሰሜኑን ጦርነት ብናነሳ እንኳን ተነጋግሮ ባለመግባባት የመጣ ነው።

እርግጥ ነው ተነጋግሮ ለመግባባት የሁለት ሀይሎች ፍቃደኝነት ያስፈልጋል። ተነጋግሮ ለመግባባት የአንድ ወገን ፍቃደኝነት ብቻውን ዋጋ የለውም። አንዱ ሰላምን እየፈለገ አንዱ ጦርነትን በሚፈልግበት ሁኔታ ላይ ተነጋግሮ መግባባት አዳጋች ነው የሚሆነው። የሀገራችን ሁኔታም ይሄን እውነት የተላበሰ ሆኖ እናገኘዋለን። ሰላም በሚፈልጉና ነውጥ በሚፈልጉ ቡድኖች መካከል ሀገር ጸንታ መቆም አትችልም። የሀገር በጸንታ እንድትቆም ሰላም ፈላጊና የሰላምን ዋጋ የተረዳ ኃይል ያስፈልጋል፤ ይሄ ኃይል መሪንም ተመሪንም የሚመለከት ነው።

አበው ሲተርቱ ባለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል ይላሉ። እውነት ነው ባለመነጋገራችን ደጃዝማችነታችንን አጥተናል። ሰላማችንን አጥተናል። ክብራችንን፣ ከፍታችንን ተነጥቀናል። ባለመነጋገራችን ወደማይገባንና ወደማይመጥነን እልቂትና ትንቅንቅ ገብተናል። የሰላም አማራጮችን እየዘጋን የመገፋፋት መንገዶችን ስንጠርግ ነበር። ይሄ አስተሳሰብ ሀገር ከማጥፋትና ታሪክ ከማበላሸት ባለፈ ለማንም አልጠቀመም። ዓለም ላይ በጦርነት የከፋ ታሪክ ያላቸውን ሀገሮች ብንመለከት ሁሉም ታሪካቸውንና መሰረታቸውን ያበላሹ ሆነው ነው የምናገኛቸው።

ሰላም በመነጋገር ውስጥ፣ ጦርነት ደግሞ በእልህና ጠበኝነት ውስጥ የሚፈጠሩ ነገሮች ናቸው። በመነጋገር ሰላምን ማምጣት እየቻልን በእልህ ወደ ጦርነት የምንገባው ነገር አይገባኝም። እንደ ሀገር ብዙ ችግሮች አሉብን፤ ሁሉም ችግሮቻችን ግን በጠረጴዛ ዙሪያ መፈታት የሚችሉ ናቸው። ከሰላም የላቀም ሆነ፤ ከሰላም እጦት የገዘፈ ችግር በዓለም የለም። ችግሮቻችን ከሰላም ተልቀው ወደ ጦርነትና ወደ ሞት እንዲወስዱን እድል የምንሰጣቸው ራሳችን ነን።

የማንክደው ሀቅ ቢኖር ሀገራችን ኢትዮጵያ በሰሜኑ ጦርነት ብዙ ኪሳራ ደርሶባታል። በቆረቆር ላይ ቁምጥና ሆኖብን ብዙ ዋጋዎችን አስከፍሎናል። በተለይ በኢኮኖሚው ረገድ ይሄ ነው የማይባል ኪሳራን አስተናግደናል። በዋናነት ኢኮኖሚን እናንሳ እንጂ ጦርነት የማይደርስበት የማህበረሰብ ክፍል የለም። በነዚህ ሁለት አመት ውስጥ በሰሜኑ ጦርነት ያልታመመ የማህበረሰብ ክፍል የለም። እርግጥ የሰሜኑ ጦርነት እንዳይነሳ መንግስት ብዙ የለፋ ቢሆንም፤ ሰላም ግን በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚሆን ባለመሆኑ በጦርነት ውስጥ ልናልፍ ተገድደናል። በዚህም ብዙ ነፍሶችን፣ ብዙ ጉስቁልናዎችን፣ ብዙ መፈናቅሎችን አስተናግደናል።

አሁን ልንረዳው የሚገባን ጉዳይ ቢኖር አንድ ነገር ብቻ ነው፤ እርሱም በጋራ ሀሳብ ሰላማዊ ሀገርን መፍጠር ነው። ሀሳቦቻችን ሰላምን እንዲወልዱ፣ አንድነትን እንዲጸንሱ እድል ልንሰጣቸው ይገባል። ሀሳቦቻችን ወደ እርቅ የሚወስዱ፣ ወደ ምክክር የሚያደርሱ መሆናቸውን ማጤን ይኖርብናል። ሀገራችን ሰላማዊ ሀሳብ አፍላቂነት ጎድሎባታል፤ ሀሳቦቻችን ሁሉ ነውጥ ፈጣሪዎች ናቸው። በተማሩትም ባልተማሩትም የሚፈበረኩ ሀሳቦች ለሀገራችን የሚበጁ ሳይሆኑ ለጥቂት ቡድኖች የሚበጁ ናቸው። ሀሳብ ስንፈጥር ሀገርና ህዝብን እያሰብን መሆን አለበት። ሀሳብ ስናስብ ወደ ማህበረሰቡ ደርሶ የሚፈጥረውን ነገር መረዳት መሆን መቻል አለበት። አሁን ላይ ሀሳቦቻችን ናቸው ወደ ጦርነትና ወዳልተፈለገ ነገር እየመሩን ያሉት።

> **ባለፉት ሁለት የጦርነት አመታት ውስጥ ኢኮኖሚያችን ምን ያክል እንደተጎዳ መረዳት እንችላለን። ጊዜው ከትላንት የምንማርበት ነው። ከሰላም ውጭ ምንም አማራጭ እንደሌለን የምንረዳበት ነው። ሀገራችን በምንም አይነት መልኩ ጦርነት የሚያስፈልጋት አይደለችም**

ለሀገር በሚበጅ ሀሳብ ውስጥ ለውጥ እንጂ ነውጥ የለም። ሰላም እንጂ ጦርነት የማይታሰብ ነው። እናም በጋራ ሀሳብ ሰላማዊቷን ኢትዮጵያ እንድንፈጥር ሰላማዊ ሀሳብ ያስፈልገናል። በሰላም ውስጥ ካልሆነ በምንም ውስጥ ማትረፍ አንችልም። ዝም እንደሚነቅዝ በማሰብ፣ ካለመነጋገር ደጃዝማችነት እንደሌለ በማወቅ ልቦቻችን ለንግግርና ለተግባቦት እንክፈት።

ለዚህ ደግሞ ሀሳብ አላጣንም፤ ሀሳብ አጥተንም አናውቅም፤ ግን በሀሳቦቻችን መካከል ሰላማዊነት የለም። እርቅና ምክክር የለም። እኔ ብለን ጀምረን እኔ ብለን የምናበቃ ነን። በሀሳቦቻችን ውስጥ እኛነት ስለሌለ ነው ዛሬ ላይ ለጦርነት ቁርሾ የበቃነው። እኛ ብለን ጀምረን እኛ ብለን የምንጨርሰው ሀሳብና ታሪክ ከሌለን አብሮ መቆም አንችልም። አብሮ የሚያቆመን፣ አብሮ የሚያኖረን የጋራ ሀሳባችን ነው። እኛ ብለን ስንነሳ ያኔ ተነጋግሮ መግባባት እንችላለን። እኛ ብለን ስንነሳ ሰላማዊ ሀገር መፍጠር ይቻለናል። ሁልጊዜም ሀሳብ ስናነሳ ኢትዮጵያን እያሰብን መሆን አለበት።

ለእኛ የሚጠቅመውን ብቻ ሳይሆን ለብዙሃኑ የሚበጀውንም ማሰብ ያስፈልጋል። ለእኛ የሚበጀን ደግሞ የሚበጀን በጋራ ሀሳብ ሰላማዊ የሆነች ሀገርን መፍጠር ነው። ሀገራችን ሰላም እስካልሆነች ድረስ መጪው ጊዜ ሁላችንንም ነው የሚያስፈራን። መጪው ጊዜ ተምረን እንድንመረቅበት፣ ሰርተን እንድንከብርበት፣ ዘርተን እንድንቅምበት፣ ወግ ማዕረግ እንድናይበት ሰላም ሊሆን ይገባል። ሰላም የሚሆነው ደግሞ በጋራ ሀሳብ የጋራ ሀገር ስንፈጥር ነው። ዓለም ላይ በጦርነት ሰላም ያመጣ ሀገር የለም። ጦርነት ሰላም የሚታጣበት ስፍራ እንጂ የሰላም መገኛ ሆኖ አያውቅም። እኛም ሰላማችንን ትንሽ ዞር ብለን እስከዛሬ ባልሞከርነው የምክክር መንገድ ፈልገን ልናገኘው ይገባል።

ጦርነት ሁሌም አንድ አይነት ነው። በሀሳብ ልዩነት ይጀመርና ብዙዎችን ለሞትና ለአካል ጉዳት ይዳርጋል። ገዳይና ሟች እስኪበቃቸው እየገደሉ የሚሞቱበት ነው። መጨረሻው ግን በእርቅ ይቋጫል። እኔ የምለው ገዳይና ሟች ሳንሆን፣ ችግርና ጉስቁልና ሳይደርስብን ወደ ጦርነት የሚወስዱንን መንገዶች እንዝጋ ነው። እኔ የምለው ሳንገል እና ሳንሞት፣ ከብዙ እልቂት በኋላ ሳንጨባበጥ ልዩነታችንን አጥበን ወደ ሰላም እንምጣ ነው። እኔ የምለው በውይይትና በምክክር በጋራ ሀሳብ የጋራ ቤት እንስራ ነው። ሰላም እንጂ ጦርነት ለማንም ጠቅሞ አያውቅም። በተለይ እንደ እኛ ሀገር በድህነትና በኋላ ቀርነት በምትማቅቅ ሀገር ላይ ጦርነት ለምንም ነገር መፍትሄ ሆኖ አያውቅም። መፍትሄዎቻችንን መነጋገር ውስጥ መፈለግ ነው የሚኖርብን።

ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት የሰሜኑ ጦርነት መልከ ብዙ ኪሳራን ነው ያደረሰብን። በምክክር ተፈትቶ ቢሆን፣ በሰላም ተቋጭቶ ቢሆን ይሄ ሁሉ ኪሳራ በሀገራችን ላይ ባልደረሰ ነበር። የሰሜኑን ጦርነት በኢኮኖሚ ላይ ምን ያክል ኪሳራ እንዳደረሰ አንድ እውነት ልንገራችሁ። ጦርነቱ ተጀምሮ የሕግ ማስከበር ዘመቻው እንደተጠናቀቀ ሰሞን መንግስት በትግራይ ክልል ከመቶ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንዳደረገ በመግለጫው ነግሮናል። ልብ በሉ መቶ ሚሊዮን አይደለም መቶ ቢሊዮን ነው። መቶ ቢሊዮን ብር አይደለም ለአንዲት ድሀ ሀገር ቀርቶ በኢኮኖሚያቸው ለፈረጠሙ ባለጸጋ ሀገራትም ቢሆን ብዙ ብር ነው።

ይሄን በምሳሌ ለማስረዳት ልሞክር፤ የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ ለስልሳ ሺ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል የፈጠረ ተቋም ነው። ይሄ ለስልሳ ሺህ ዜጎች የስራ እድል የፈጠረው ተቋም በአንድ ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር የተገነባ ነው። ልብ በሉ መንግስት በሰሜኑ ጦርነት ለዛውም በጥቂት ወራት ውስጥ መቶ ቢሊዮን ብር ወጪ አውጥቷል። የሀዋሳ ኢንዱስትሪያል ፓርክ በአንድ ቢሊዮን ብር ተገንብቶ ለስልሳ ሺህ ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል። በጦርነቱ የወጣው መቶ ቢሊዮን ብር መቶ ኢንዱስትሪያል ፓርክን ወይም ደግሞ ሌሎች ፋብሪካዎችን ገንብቶ ለበርካታ ስራ አጥ ዜጎች እንጀራ መሆን ይችል ነበር። ይሄን ሀሳብ ያነሳሁት ጦርነት ከኪሳራ በቀር ምንም እንደሌለው ለማስረዳት ብዬ ነው።

ከዚህ እውነት በመነሳት ባለፉት ሁለት የጦርነት አመታት ውስጥ ኢኮኖሚያችን ምን ያክል እንደተጎዳ መረዳት እንችላለን። ጊዜው ከትላንት የምንማርበት ነው። ከሰላም ውጭ ምንም አማራጭ እንደሌለን የምንረዳበት ነው። ሀገራችን በምንም አይነት መልኩ ጦርነት የሚያስፈልጋት አይደለችም። ድህነት የቀደዳቸው፣ ማጣት ያጎበጣቸው ብዙ ቀዳዳዎች አሉብን። እነሱን መድፈን እንጂ በሆነ ባልሆነ ጦር መማዘዝ አሁን ላለንበት ሀገራዊ ሁኔታ የሚመች አይደለም። በሰላም ሀሳብ ወደፊት መሄድ ብቻ ነው የሚያዋጣን። ችግሮቻችን፣ ድህነቶቻችን፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ነውሮቻችን በሰላማዊ መንገድ ካልሆነ በሌላ በምንም እንዳይፈቱ ሆነው የተተበተቡ ናቸው።

ረጋ ካልን ዝግ ካልንና ከሰከንን የምንፈታቸው ብዙ ቋጠሮዎች አሉ። በሰላም የማይፈታ ቋጠሮ የለም። ጦርነት ቋጠሮ ያጠብቃል እንጂ ቋጠሮ አይፈታም። ዛሬ ላይ የምንገዳደልባቸው ችግሮችም በትላንት ፖለቲካ፣ በትላንት እኔነት የተቋጠሩ ናቸው። ቋጠሮዎቻችም እንዲላሉ የሰላም አማራጮችን መመልከት አለብን። ጦርነት ምን ያክል አስከፊ እንደሆነ ያለፉ ታሪኮቻችን ምስክሮቻችን ናቸው። እነሱን እማኝ አድርገን ወደ ሰላም እንጂ ወደ ነውጥ መመለስ አይኖርብንም።

በጋራ ሀሳብ የሰላም ሀገር መገንባት ቀጣዩ የቤት ስራችን ነው። በተጀመረው የሰላም ጥላ ስር ብዙ የኢትዮጵያ ህልሞች አሉ። የኢትዮጵያ ህልሞች የእኔና የእናንተ ህልሞች ናቸው። የእኔና የእናንተ ህልሞች ደግሞ የትውልዱ ህልሞች ናቸው። ሀገር የምትፈጠረው በዚህ እውነት ውስጥ ነው። ህልሞቻችን ሰላም ሲለብሱ የኔ ሀገር ትፈጠራለች። ያኔ ሁሉም ነገር መስተካከል ይጀምራል። ህልሞቻችን ነፍስ የሚዘሩት ደግሞ ኢትዮጵያ ሰላም ስትሆን ነው። በብቻ ሀሳብ ነውጥ ያነገበች ሀገር ፈጥረን ለራሳችንም ለሌሎችም መከራ ሆነን ሰንብተናል። አሁን ግን የይበቃል ጊዜ ላይ ነን። በጋራ ሀሳብ የሰላም ሀገር የምንፈጥርበት ጊዜ ላይ ነን። የኢትዮጵያ ህልሞቻ እውን ሊሆኑ ይገባል። ሰላምን ለብሰው፣ አንድነት ተዋህደው መሬት መንካት አለባቸው። ይሄ እንዲሆን እኛ የሰላም ሰዎች ልንሆን ይገባል። ስለ ሰላም እያወራን፣ በሰላም መኖርን ባህል ልናደርግ ይገባል።

ከፊታችን የኢትዮጵያን ከፍታ የሚያረጋግጡ ብዙ ነገሮች እየመጡ ነው። ከዚህ ውስጥ አንዱ ስለሰላም የምናወራበት፣ ስለአንድነት የምንመካከርበት ሀገራዊ ምክክር ነው። እንዳየነው፣ እንደሰማነው፣ እንደደረሰብን፣ እንደተጎዳነው፣... ጥቂት ሰላም ሳይሆን ብዙ ሰላም ነው የሚያስፈልገን። ብዙ ሰላም እንዲመጣልን ደግሞ ሁላችንም የበኩላችንን መወጣት ይጠበቅብናል። በአንድ ሀገር ላይ አንድ አይነት ሀሳብ ብቻ ኖሮ አያውቅም። ሀገር በአንድ አይነት ሀሳብ ብቻ ተመርታ አታውቅም። ለሀገር የሚያስፈልጉ ሀሳቦች ከዚም ከዛም የተውጣጡ ዘርፈ ብዙ እና ሰላማዊ ሀሳቦች ናቸው። ሀሳብ ችግር የሚሆነው ነውጥ ሲቋጠር ነው። በሀገራችን ላይ እንደ ብዝሃነታችን ልዩ ልዩ ሀሳቦች መነሳታቸው ችግር የለውም። ችግር የሚሆነው እነዛ ልዩ ልዩ ሀሳቦች በምክክርና በውይይት አንድነትን መልበስ ካልቻሉ ነው። ሆኖም ህልሙን ሀገሩ ያደረገ ፖለቲከኛ በምንም ልዩነት ውስጥ መግባባት ይችላል። አላማውን ህዝብ ያደረገ ዜጋ በምንም የሀሳብ ልዩነት ውስጥ ወደ አንድነት የማይመጣበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ተነጋግረን የማንግባባው፣ አውረተን የማንስማማው ከሀገርና ህዝብ የተደበቀ ሌላ የኔነት አላማ ሲኖረን ነው።

የኢትዮጵያ ህልሞች እንዲሰምሩ ልዩ ልዩ ሀሳቦችን የሚያስታርቅ የአንድነት ወግና ባህል ያስፈልገናል። ከነበርንበት የጦርነት ታሪክ ለመውጣት ተነጋግሮ የመግባባት፣ ተግባብቶ አብሮ የመኖር ስልጣኔ ያስፈልገናል። የሀገራችን ሰላም እኛ እጅ ላይ ነው ያለው። እጆቻችንን ለሰላም ስንዘረጋ፣ አንደበቶቻችንን ለእርቅና ለምክክር ስንከፍት ያኔ ሰላማችን ይፈጠራል። በአንድነት ከቆምን ከእኛ ርቆ ለሌሎች የተረፈ ብዙ ሰላም ያለን ሕዝቦች ነን። ብዙዎችን በሰላማችን አርቀንና አስታርቀን ቀን አውጥተናል። ያ ብዙ ሰላም ዛሬ ላይ ያስፈልገናል፤ እናም በሰላማዊ ሀሳብ ሰላማዊ ሀገር እንገንባ።

ኢኮኖሚ

ግብርና

# የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት አቅራቢዎችን ፍላጎት የመመለስ ጥረት

**ስምስም መንግሥቱ**

በኢትዮጵያ የምርትና ምርታማነት ጉዳይ ሲነሳ ግብርናን ማዘመን ቀዳሚ ጉዳይ ሆኖ ሲጠቀስ ቆይቷል። ለዚህም ምክንያቱ በበሬ ጫንቃ አርሶ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንዲሁም በአጠቃላይ ሀገር ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ልታገኝ ስለማትችል ነው። ከግብርናው የሚጠበቀውን ለማግኘት ሜካናይዜሽን ላይ መሥራት አንዱ አማራጭ ስለመሆኑም የዘርፉ ባለሙያዎች ሲመክሩ ኖረዋል።

ይህን ሀሳብ መሬት ለማውረድ፤ መንግሥት ለምርትና ምርታማነት እድገት ወሳኝ በሆኑት ግብርናውን በማዘመን፣ ዝናብ ጠብቆ ግብርናን ከማካሄድ በተጓዳኝ እንደ መስኖ ባሉት አማራጮች ላይ አተኩሮ መሥራት ውስጥ ገብቷል፤ በዚህም ውጤቶች እየታዩ ናቸው። በመንግስት በኩል የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎችን በስፋት መጠቀም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ናቸው።

በአሁኑ ወቅትም ብርቱ አርሶ አደሮች በግላቸው፣ ሌሎች ደግሞ በአርሶ አደሮች የህብረት ሥራ ማህበሮቻቸው ትራክተሮችንና ኮምባይነሮችን እየገዙ ለግብርና ሥራቸው እያዋሉ ናቸው። የአርሶ አደሩ የማሽነሪ ፍላጎቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ የማሽነሪ አከራዮችም መፈጠር ጀምረዋል።

የሜካናይዜሽን ማሽነሪ አከራዮች አርሶ አደሮች በቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እያደረጉ ናቸው፤ እነርሱም በሚሰጡት የኪራይ አገልግሎት ገቢ በማግኘት የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ችለዋል።

የግብርና ቴክኖሎጂ የሰው ድካምን ከመቀነስና ጊዜን ከመቆጠብ በተጨማሪ በግብርና ሥራ ወቅት መሬትን በደንብ በመገልበጥ፣ በአጨዳ፣ በዘር መሰብሰብና በውቂያ የሚባክን ምርትን በመቀነስ ፋይዳው የጎላ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።


እንዲህ ዘርፈ ብዙ ጥቅም እያስገኘ ያለው የግብርና ቴክኖሎጂ በማህበር በተደራጁ ወይንም የገንዘብ አቅም በፈጠሩ አርሶ አደሮች ካልሆነ በስተቀር በአርሶ አደር አቅም ለመግዛት የሚቻል እንዳልሆነ ይታወቃል። በኪራይ አገልግሎቱን የማግኘት አማራጭ በመኖሩ እያንዳንዱ አርሶ አደር ቴክኖሎጂውን መግዛት አይጠበቅበትም።

በዚህ ወቅትም ቴክኖሎጂው በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘው ወይንም እየቀረበ ያለው በኪራይ አገልግሎት በሚሰጡ አካላት ነው። የኪራይ አገልግሎቱ የሚሰጠውም በማህበር በተደራጁ አካላትና በግለሰብ አቅራቢዎች በመሆኑ አርሶ አደሩ ተመጣጣኝ ኪራይ አቅራቢዎችን ለመምረጥ አማራጭ ተፈጥሮለታል። የቴክኖሎጂ አቅርቦቱ እየጨመረ ሲሄድ ደግሞ የአገልግሎት ተመጣጣኝነት እየተሻሻለ ይሄዳል።


በግብርና ቴክኖሎጂ የመጠቀም የፍላጎት ማደግን መሠረት በማድረግ ግብርና ሚኒስቴር በየግላቸው እንደ ትራክተር፣ ኮንባይነር ሀርቨስት (ሰብል አጭዶ የሚወቃ መሣሪያ)፣ ሌሎችም የግብርና ቴክኖሎጂ ገዝተው የኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችና ግለሰቦች በማህበር ተደራጅተው በጋራ አቅም ፈጥረው አገልግሎቱን እንዲሰጡ የማስተባበር ሥራ እየሰራ ይገኛል። ከ270 በላይ የሆኑ አባላትን የያዘ ኢትዮጵያ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጭዎች ማህበር ተመስርቶ የተናበበ ሥራ ለመሥራት እንዲሁም ድጋፍና ክትትል ለማድረግ መቻሉን፣ አገልግሎት አቅራቢዎችም በየግላቸው አገልግሎት ሲሰጡ ያጋጥማቸው የነበረውን ችግርና ከመንግሥትም የሚፈልጉትን ድጋፍ ለማግኘት እንዳስቻላቸው እንዲሁም የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደተቻለ የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል።

ፍላጎትን ለማሟላት ደግሞ አገልግሎት ሰጭዎች ቴክኖሎጂውን በብድር መግዛት እንዲችሉና ከቀረጥም ነፃ እንዲሆን መንግሥት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። እንዲህ ያሉ የመንግሥት ድጋፎች ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግብርና ቴክኖሎጂ አስፈላጊነት ታምኖበት ትኩረት እንደተሰጠው አንዱ ማሳያ ነው።

ካለፉት ሁለት አመታት ወዲህ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ በግዥ በስፋት ወደ ሀገር ውስጥ እየገባ መሆኑን፣ የቴክኖሎጂ አገልግሎት በሚያቀርቡ አካላት ያለው የግዥ ፍላጎትም ሆነ በአርሶ አደሩ በኩልም በቴክኖሎጂ ለመጠቀም ያለው ተነሳሽነት እየጨመረ መምጣቱን የኢትዮጵያ ልማት



ዶክተር ዮሀንስ አያሌው



አቶ አሳዬ ከበደ



ባንክ ሰሞኑን ለሊዝ ፋይናንስ ደንበኞች ያቀረባቸውን የአጭዶ መውቂያ የግብርና ማሽኖች ርክክብ በተደረገበት ወቅት ለመገንዘብ ችለናል። ባንኩም ሆነ የባንኩ አምስተኛ ዙር ተረካቢ ደንበኞችም በወቅቱ ይህንኑ አረጋግጠዋል።

በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ የዋሉት ትራክተሮች 12ሺ ብቻ እንደነበሩ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝደንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው በዚሁ የርክክብ ሥነስርአት ላይ አስታውሰዋል። መንግሥት የግብርና ሜካናይዜሽን ፕሮግራም መተግበር ከጀመረ ከሁለት አመታት ወዲህ ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ትራክተሮች ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጉን ገልጸዋል። ፕሮግራሙ መተግበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ 13 ሚሊዮን ዩሮ ተመድቦ ቁጥራቸው 89 የሚደርስ የተለያዩ የግብርና መሣሪያዎች ተገዝተው መቅረባቸውንም አመልክተዋል።

ዶክተር ዮሐንስ እንዳሉት፤ በዚህ ጥቂት ጊዜ ውስጥም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ለማቅረብ ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ሆኗል። እስካሁንም 530 ያህል ጥያቄዎች ለባንኩ ቀርቧል። የቀረበው ጥያቄም በገንዘብ ወደ 82 ሚሊየን ዩሮ የሚያወጣ ነው። ይህም 13 ሚሊየን ዩሮ የጀርመን መንግሥት፣ ሁለት ሚሊየን ዩሮ ደግሞ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚሸፈን እንደሆነና ቀሪውን ለማሟላት የተለያዩ መንገዶች እየተሞከሩ እንደሆነና ተስፋ መኖሩን አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ በአነስተኛ አርሶ አደሮች የተያዘ መሬት ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። እነዚህ አነስተኛ የእርሻ መሬት የያዙ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ሳይፈናቀሉ ግብርናውን ማዘመን (ትራንስፎርም) ማድረግ ካስፈለገ አማራጩና መፍትሄው የግብርና ሜካናይዝሽንን ጥቅም ላይ ማዋል ነው። በተለይም በኩታ ገጠም (ክላስተር) የተጀመረውን የግብርና ዘዴ በሜካናይዝሽን እንዲታገዝ ማድረግ ውጤታማ ያደርጋል። ውጤቱም ከወዲሁ መታየት እንደጀመረም ዶክተር ዮሐንስ ይገልጻሉ። ጥቅም ላይ እየዋሉ ባሉ የእርሻ ትራክተር፣ አጭዶ በሚወቃ ማሽን እየተከናወነ ያለው ልማት ለግብርናው መዘመን አስተዋጽኦ በማበርከት ክፍተቶችን መቅረፍ እንደተቻለ ባንኩ ማረጋገጥ መቻሉንም አመልክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ መዋሉ በግብርናው ሥራ ላይ የሚሰማራውን ሰፊ የሰው ኃይል ለሌላ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማዋል የሚቻልበትን እድል ይፈጥራል፤ በተለይም አርሶ አደሩ በሚያገኘው ትርፍ ጊዜ ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝለት ሥራ ላይ ለመሰማራት ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

በግብርና ሥራ ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው የሚስተጓጎሉ ተማሪዎችንም ችግር ይፈታል። ጊዜና ጉልበት ተቆጥቦ ለሌላ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሲውል በምጣኔ ሀብት እድገት ከፍ ያለ ሚና ይኖረዋል።

እነዚህን ውጤቶች ለማስመዝገብ የተጀመረው የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትና ሰፊ የቤት ሥራም እንደሚጠበቅ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ሰፊ ሥራ ለመሥራት የተለያዩ ጥረቶች በማድረግ ላይ እንደሆነም ተናግረዋል።

በእለቱ የአጭዶ መውቂያ የግብርና ሜካናይዜሽን ከተረከቡት በግላቸው የኪራይ አገልግሎት ሰጭዎች መካከል አንዱ አቶ አሳዬ ከበደ ናቸው። ነዋሪነታቸው ባሌ እንደሆነና የኪራይ አገልግሎቱንም በአካባቢያቸው ለመስጠት እንደተዘጋጁ ነው የነገሩን። አቶ አሳዬ እንደገለጹልን፤20 በመቶ ቅድሚያ ክፍያ ፈጽመው፣ ቀሪውን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባመቻቸላቸው በአምስት አመት የጊዜ ገደብ ተከፍሎ በሚመለስ ብድር መሠረት GC 590 ጉልበት ያለው ኮንባይነር ነው የተረከቡት። ዋጋውም 11 ሚሊዮን ብር እንደሆነ ነግረውናል።

አቶ አሳዬ ልማት ባንኩ ባመቻቸው ብድር የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽን ግዥ ሲፈጽሙ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። ማሽኑ እንደየሰብሉ አይነት መሳሪያዎችን በማቀያየር አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው። በዚህ ዘዴ የተለያዩ ሰብሎችን አጭዶ ሰብስቦ ማጓጓዝ ይቻላል። ቀደም ሲል የገዙት ማሽን ዋጋ አራት ሚሊዮን ነበር። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ከእጥፍ በላይ ጨምሯል። አዲስ የተረከቡት ማሽን ግን በፈረስ ጉልበቱ እንዲሁም ፍጥነቱና በቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ ቀድሞ ከገዙት ማሽን የተሻለ ሆኖ ነው ያገኙት።

የፈረስ ጉልበቱ ሲጨምር በብዛት እህል ለመሰብሰብ ያስችላል። ካሜራም የተገጠመለት መሆኑ ደግሞ እይታን ከሚጋርዱ ነገሮች ነጻ በሆነ ማሽኑን እንደልብ በማሣ ውስጥ ለማንቀሳቀስ ያስችላል። ለደህንነት የሚጠቅም ነገርም የያዘ በመሆኑ በቴክኖሎጂ የተሻለ ነው ሲሉ አቶ አሳዬ ያብራራሉ።

ቀደም ሲል የገዙት ማሽን ግን GC 580 ነበር። አዲሱን ማሽን በፈለጉት ወቅት አላገኙም። መክፈል የሚጠበቅባቸውን ክፍያ እንደፈጸሙ በአጭር ጊዜ በተለይም የመኸር ሰብል ለመሰብሰብ ይደርሳል ብለው ጠብቀው ነበር። የደረሳቸው ታኅሣሥ መጨረሻ ላይ ነው። ሥራ የተገባደደበት ጊዜ መሆኑን ነው የገለጹት።

ማሽኑ የዋጋ ጭማሪ ሲኖረው ለአርሶ አደሩ የሚሰጠው የኪራይ አገልግሎት ላይም የዋጋ ጭማሪ እንደሚኖረው ይገመታል። ከዚህ አንጻርም ስላለው ሁኔታ አቶ አሳዬ እንደነገሩን እስካሁን በተለያየ ዋጋ የኪራይ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ቢሆኑም በ2014-2015 የምርት ዘመን በአንድ ኩንታል 150 (አንድ መቶ ሃምሣ) ብር ሂሣብ ነው አገልግሎት የሰጡት። የነዳጅና የተለያዩ ወጪዎች ስላሉ ወደፊት የሚሆነውን ለመገመት ያስቸግራል ነው ያሉት።

አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂው የምርት ብክነትን እያስቀረላቸውና የተለያየ ጥቅምም በማየቱ አገልግሎቱ እንዲቀርብለት ፍላጎት እንዳለው አቶ አሳዬ ጠቅሰው፣ እስካሁን ባለው አገልግሎትም በግላቸው መልካም ሆኖ እንዳገኙት ይናገራሉ።

አቶ አሳዬ ከአርሶ አደሩ ጋር በአገልግሎት መልካም ግንኙነት እንዳላቸው ቢገልጹም ለገበያ ሽሚያ ሲባልና ለነዳጅ ቁጠባ የግብርናው ሥራ በሚጠይቀው አግባብ በተለይ በአጨዳ ወቅት በትክክል ካለመፈጸም ጋር በተያያዘ አርሶ አደሩ በአገልግሎት ሰጭዎች ላይ ቅሬታ ይቀርባል። እርሳቸው አገልግሎት በሚሰጡበት ባሌ አካባቢ በአመት ሁለት ጊዜ ምርት በሚሰበሰብበት ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ በመጀመሪያ ቢያበላሹ በሁለተኛው አገልግሎታቸውን ፈልጎ የሚመጣ አርሶ አደር እንደማይኖር ስለሚገነዘቡ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ነው ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ ይገልጻሉ። በእዚህ በኩል እስካሁንም ችግር ያልገጠማቸው መሆኑን ተናግረዋል።

የኪራይ አገልግሎቱን በባሌና አርሲ አካባቢዎች ነው እየሰጡ ያሉት። ወደሌላ አካባቢ በመሄድ አገልግሎት ለመስጠት የማሽኑ አካላት መፍታት እንደሚያስፈልግና ሌላ ማጓጓዣ መጠቀም እንደሚገባ ይናገራሉ፤ ለመጫኛ የሚወጣው ወጪም ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ግብርናውን ለማዘመን የተያዘውን እንቅስቃሴ ለማጠናከር ማሽኖችን በስፋት ማቅረብ ይጠበቃል። በአቅርቦት በኩል መዘግየት ከተፈጠረ ምርታማነትን በሚፈለገው ፍጥነት ለማሳደግ ካለማስቻሉ በተጨማሪ የማሽን ዋጋ እንዲጨምር ያደርጋል። የማሽን ዋጋ ሲጨምር ደግሞ በሚሰጠው በግብርና ሥራ የኪራይ አገልግሎት ላይ የዋጋ ጭማሪ ወይም መናር በማስከተል የአርሶ አደሩን የመክፈል አቅም ሊፈታተን ይችላል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝደንት ዶክተር ዮሐንስ በሰጡት ማብራሪያ፤ መዘግየትን ከእርሻና የሰብል መሰብሰብ ወቅቶች ጋር በማያያዝ ካልሆነ በስተቀር መዘግየት አልተፈጠረም። ኤልሲ ከተከፈተ በኋላ ከሶስት ወር በላይ አይቆይም። አምስት ዙሮች መድረስ የተቻለው በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ ነው።

ስድስተኛውም ዙር ተጀምሯል። ግዥው የሚፈጸመው ገዥው በሚያመለክተውና ባንኩ በሚያመቻቸው ነው። የገንዘብ ድጋፍ (ፈንድ) የሚለቀቀው ለመግዛት የሚያስፈልገው ሂደት እንደተጠናቀቀ ነው።

በዚህ የግብርና ሜካናይዜሽን ድጋፍ እስካሁን ከጀርመን መንግሥት ጋር ባለው ስምምነት እየተፈጸመ እንደሆነና ከሌሎች አጋሮች ጋርም በጋራ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑንና ተስፋ ሰጭ ነገሮች መኖራቸውንም አመልክተዋል። እስካሁን በተገዙት ማሽኖች በተሰራው ሥራም ለጋሾች ደስተኞች መሆናቸውንና ይህም ለቀጣይ ድጋፍ በጎ ምላሽ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል።

በግዥ እየገቡ ስላሉት ማሽኖች ዘመናዊነትም እንዳስረዱት፤ ማሽኖቹ በዓለም ላይ የተሻሉ፣ ለረጅም ጊዜም አገልግሎት የሚሰጡ ለኢትዮጵያ መሬት ተስማሚ ናቸው። ግዥ ከመፈጸሙ በፊት ማሽኑ ለኢትዮጵያ መሬት ተስማሚ መሆኑ ጥናት ይደረጋል። በጥናት ሥራው ግብርና ሚኒስቴርም ተሳታፊ ነው። ግዥው የሚፈጸመውም አቅራቢዎች ተወዳድረው በመሆኑ በጣም የተሻለው ተመርጦ ነው የተገዛው።

በልማት ባንኩ የብድር አመቻችነት ወደ ሀገር ገብተው ለአገልግሎት የበቁት የግብርና ሜካናይዜሽን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተለይም በባሌ፣ አርሲ፣ ሻሸመኔ፣ ቡሬ፣ አላባ ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውንም ከልማት ባንኩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ሳንባዲና

ጽጌረዳ ጫንያለው

ዓይኖቼ አያዩም ብርሃን የላቸው
በልጅነቴ ድሮ አጥቻቸው
ልቤን ተሰማው እንግዳ ነገር
ምርኩዝ ይዤ ነው የሚያውቀኝ ሀገር
ዓለም ታየቺኝ ባንቺ ውስጥ ሆና

በፍቅር ኩራዝ በላምባዲና እንዲል ቴዲ አፍሮ በሙዚቃው ለአይነ ስውራን የፍቅር፣ የእውቀት ላምባዲና የሆነው ትምህርት ቤት መከፈቱን ስንሰማ ወደዚያ ተጓዝን። ይህ የልጅነት ዓይኖቻቸውን ብርሃን ያደረገላቸው ትምህርት ቤት ሁለት ነገሮችን እንደሀገር የያዘ መሆኑን አውቀናል። የመጀመሪያው በየአቅጣጫው እንዳጣራነው የአይነ ስውራን ትምህርት ቤት በሀገር ደረጃ በመዋዕለ ሕፃናት ደረጃ የለም። እናም የመጀመሪያው ሆኖ የመጀመሪያውን ተስፋ እየሰጣቸው ይገኛል።

እስከዛሬ ባለው ሁኔታ አይነ ስውራን ትምህርት የሚያገኙት እንደ እኩዮቻቸው በአራት ዓመት እድሜያቸው ገብተው አይደለም። ከፍ ካሉ በኋላ በአዳሪ ትምህርት ቤት አለያም በአንደኛ ደረጃ በአካቶ ትምህርት መልኩ ነው። ይህ ደግሞ በልጅነታቸው የሚያገኙትን እውቀት ሳያገኙ እንዲያልፉ ያስገድዳቸዋል።

በመዋዕለ ህጻናቱ ከመከፈት ብቻቸውን ሆነው በሚፈልጉት መልኩ እየተማሩም በመሆኑ ተስፋቸው እየለመለመላቸው ነው። በእርግጥ ትምህርት ቤቱ ለሁሉም ተደራሽ፤ ሁሉንም አይነ ስውራን ሕፃናትን የሚያስተናግድ አይደለም። ምክንያቱም ገና ጀማሪ፤ በቁሳቁስ ያልተሟላ ነው። በዚያ ላይ ተስፋን በሰነቁ እናቶች፣ በተቸገሩና ልጆቼን የት ላስገባና ላስተምራቸው ብለው በተንከራተቱና በተጨነቁ ወላጆች አማካኝነት የተመሰረተ ስለሆነ ከእነርሱ አልፎ ሌሎችን ለማስተናገድ አይቻለውም። ሆኖም አንድ ቀን ግን ለሁሉም አይነ ስውራን እንደሚደርስ ይታመናል። እንደሀገርም ለህጻናት አይነ ስውራን ዕውቀት የሚያስጎበኙ መዋዕለ ህጻናት እንዲበራከቱ በር ይከፍታል የሚል እምነት ያጭራል።

መስራቾቹ አምስት እናቶች ሲሆኑ፤ ከቦርድ አመራሮች ጋር ሲደመሩ ሰባት ናቸው። ነገር ግን እንደ ጅማሮ በጥሪ ሂደት ላይ ይገኛሉ። ከ37 በላይ ልጆችን በትምህርት ቤቱ ተቀብለው ያስተናግዳሉ።

የአመሰራረቱ መነሻ በበጎ አድራጎት ድርጅት ስም ነው። ቪዥን የአይነ ስውራን በጎ አድራጎት ድርጅት በሚል የተለያዩ ሥራዎችን ተቀራርበው በሚሰሩበት ጊዜ ይህ ሀሳብ በውስጣቸው አቃጨለ። የቤታቸው ጎዶሎ ደግሞ ይበልጥ ጠንክረው እንዲሰሩበት አደረጋቸው። በተለይም በልጆቻቸው ምክንያት በቤታቸው የሚቀመጡ እናቶች ብዙዎችን ያሳስባቸው ነበር። እናም አንድ ቀን ወይዘሮ ትዕግስት ካሳ ልጆቻችን ለምን መማሪያ ያጣሉ፤ ለምንስ እኛ ከቤት ወጥተን ተጨማሪ መስራት አንችልም በሚል ተነሱ።

እርሳቸው በሙያቸው ኢንጅነር ቢሆኑም እንደልባቸው ሁለቱን አይነ ስውራን ልጆቻቸውን ትተው መስራት አይችሉም። በዚያ ላይ ለእነዚህ ልጆች በእድሜያቸው የሚማሩበት ትምህርት ቤት ቢፈልጉም የለም። እናም አቋም ይዘው ሥራውን ለመጀመር ብዙ ጓደኞቻቸውን ወደማማከሩ ገቡ። በቀላሉ ማድረግ ግን አልቻሉም። የሚያገኙትም ምላሽ እንደጠበቁት አልሆነላቸውም። ገሚሱ ባይሞክሩት እንደሚሻል ይነግሯቸዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ መንግስት ያልቻለውን እንዴት በእናንተ አቅም ትችሉታላችሁ የሚሉ ተስፋ አስቆራጭ ሃሳቦች አቅርበውላቸዋል። ጥቂቶች ደግሞ መልካም ነው ለእኛ ባይሆን ለልጅ ልጆቻችን ይደርሳል ይላል። ሆኖም ተስፋ ያልቆረጡት ወ/ሮ ትዕግስት ጉዟቸውን ወደፊት ቀጠሉ።

ልጆቻችን መውደቂያ ማግኘት አለባቸው፤ በእውቀት እንደሌሎች እኩዮቻቸው መጎልበት ይገባቸዋል ሲሉም ከድርጅት ሥራቸው በተጓዳኝ ትምህርት ቤቱን ለማቋቋም የእያንዳንዱን ደጅ አንኳኩ። የተወሰኑት በራቸውን ከፈቱላቸውም። በዚህም ቪዥን የአይነ ስውራን ትምህርት ቤትን በ2014 ዓ.ም ኅዳር ላይ ሕጋዊ እውቅና አገኘ። ትምህርት ቤቱን በዳሬክተርነት እየመሩም ዛሬ ላይ ደርሰዋል።

አንድ የትምህርት ተቋም ሲመሰረት ማሟላት የሚገባቸው መሰረታዊ ነገሮች አሉት። አንዱ የሥርዓተ ትምህርት ጉዳይ ሲሆን፤ ትምህርቱ እንደ ሀገር የተጀመረ ስላልሆነ የተሰጣቸውን እውቅና መሰረት አድርገው ማለትም ትምህርት ቢሮን የትምህርት ስርዓቱን በምን መልኩ እንደምናስኬደው ጠይቀን የተባለውን ለመተግበር ሞክረናል። ይህም የመጀመሪያ በመሆኑ በአዲስ መልኩ እስኪጀመርና አዲስ ካሪኩለም እስኪበጅለት ድረስ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ስነ ዘዴ ተጠቀሙ የሚል ነው። እናም በመደበኛ የትምህርት ስነ ዘዴ ጀምረው ከተለያዩ አካላት ተሞክሮዎችን በመውሰድ እያስተማሩ ይገኛሉ። በተለይ የውጭ ሀገራት ተሞክሮችን በአግባቡ ተጠቅመውበታል።

የማስተማር ስነ ዘዴያቸው እንደ መደበኛው የመዋዕለ ሕጻናት ትምህርት ቤት ነው። አይነ ስውር ናቸው ብለን ብሬል ትምህርት ላይ ብቻ አናተኩርም። ምክንያቱም ብሬን ማንበብና መጻፍ እውቀት አይደለም። ማንም ከተማረው ሊለምደውና ሊተገብረው የሚችል ነው። ስለሆነም ከዚያ ባሻገር ያሉ ትምህርቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል። ምክንያቱም ይህ ካልሆነ ከዚህ ሲወጡ በእጅጉ ይጎዳቸዋል። በአካቶ ትምህርት እንኳን መቀጠል አያስችላቸውም። የመምህራን ብቃት ጉዳይም እንዲሁ አንዱ መስፈርት ነውና በእነርሱ ትምህርት ቤት የተቀጠሩት አምስት መምህራን የልዩ ፍላጎት የትምህርት መስክ ተመራቂዎችን አድርገዋል። ደረጃቸውም ከዲፕሎማ እስከ ዲግሪ የደረሰ ነው።

‹‹ልጆቼ ሄራንና ሶልያና የማየት ችግር እንዳለባቸው የታወቀው ገና ዓመት ሳይሞላቸው ነው። እናም የት እንደማስገባቸው እያሰብኩ ቆየሁ። እንደእኔ የተጨነቁትንም ሳማክር ጭንቀታችን መፍትሄን ወለደ። ጠንካራ ሀሳቦችን ወደማመንጨቱ ገባንም። ልጆቻችንን በመጠቀም በሶሻል ሚዲያ እንቅስቃሴ ጀመርን። ለዚህ ደግሞ ዶንኪ ቲዩብ እጅግ በጣም አግዞናል። አንዳንድ በጎ አድራጊ ግለሰቦችን ከጎናችን እንደሆኑ ቃል ገቡልን። በእነርሱ ብርታትም ትምህርት ቤቱን ከፈትነው። ብዙ ርቀትም ተጓዝን›› የሚሉት ወይዘሮ ትዕግስት፤ ትምህርቱን ሲጀምሩ 31 ተማሪዎች ተቀብለው ማስተማር መጀመራቸውን ይናገራሉ። ሆኖም አሁን በመከታተል ላይ ያሉት 18ቱ ብቻ መሆናቸውን ያስረዳሉ። ለዚህ ደግሞ ትምህርት ቤቱ አንድ ቦታ ላይ ጀሞ አካባቢ ብቻ ነው። ከየአቅጣጫው የሚመጡ ልጆች ደግሞ ይህንን እድል መጠቀም አልቻሉም። በጣም ርቀት አለው። ይህም ቢሆን ቋሚ ገቢ ስለሌለን የአንድ ልጅ ወጪን በመሸፈንና የቤት ኪራያችንን በመሸፈን በጎ አድራጊ ግለሰቦች በመደገፋቸው ነው ዛሬ ላይ የቆምነው።

እናም አሁንም የብዙዎች እገዛ ያስፈልገናልና ይዩን ሲሉ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ።

የሕጻናት ህልም ገደብ አልባ ነው። ፍላጎታቸውም የተለያየ ነው። ይህንን ሕልማቸውን እውን ለማድረግ ደግሞ በተለያየ መልኩ ማገዝ ያስፈልጋል። ለአብነት ከህክምና ተቋማት ጋር አብሮ መስራት። ትንሽ እገዛ ካገኙ ማየት የሚችሉና ተስፋቸውን መኖር የሚችሉ ልጆች ይኖራሉ። ህጻናቱ ለነገ ብቁ ዜጎች እንዲሆኑ የህክምናና የስነልቦና አማካሪም ያስፈልጋቸዋል።

ትምህርት ቤቱ ብዙ ህልምን ሰንቆ የተነሳ ነው። በመዋዕለ ሕፃናት አልፎ እስከ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የመከፈት ርዕይ አለው። ደረጃ በደረጃ መንግስት የሚያግዘው ከሆነ ለሁሉም አይነስውር ሕፃናት መድረስ ይፈልጋል። አሁንም የማህበረሰቡ ቤት እንደሆነ ነው የሚታሰበው። ምክንያቱም የቆመው በእነርሱ ስለሆነ። ጀማሪ በመሆኑ ገደበው እንጂ ሁሉን አሳታፊ ማድረግን ይሻል። ለዚህ ግን የሚመለከተው አካል ሁሉ ሊያግዘው ይገባል። የመጀመሪያው ከየቤት ኪራይ ነጻ የሚወጣበትን መንገድ የሚመለከተው አካል ሊፈታለት ይገባል። ከዚያ ደግሞ እንደ አይነ ስውርነታቸው የመማሪያ ቁሳቁሶች ያስፈልጋቸዋልና በተቻለ መንገድ ለማሟላት ሁሉም መተጋገዝ አለበት።

ተቋሙ የመስራቾች ብቻ ሆኖ እንዳይቆይ በመጀመሪያ ደረጃ መንግስት ኃላፊነቱን ወስዶ ሊሰራበት ይገባል። ምክንያቱም መንግስት መጀመር የነበረበትን ተግባር ነው ግለሰቦች ዳዴ እንዲል ያደረጉት። እናም ማንም ሰው አይነስውር ልጅ ሊኖረው ይችላልና ለእድሜያቸው የሚመጥን ትምህርት ቤት እንዲኖራቸው መጀመሪያ መንግስት ከዚያም ግለሰቦች ተደጋግፈው ይህንን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ትምህርት ቤቶችን መክፈት እንዳለባቸውም ያሳስባሉ ወይዘሮ ትዕግስት።

ትምህርት ቤቶች የወደፊቱን ሕይወት የምንቀይስበት፤ የመጀመሪያዎቹን ፊደላት የምንለይበት ተቋም ነው፤ አይነስውራን የሀገር ተስፋ እንዲሆኑ የምናደርግበትም ነው። ስለዚህም የመንግስት ተቋማት ማለትም ትምህርት ሚኒስቴርና ትምህርት ቢሮዎች ለዚህ ፈርቀዳጅ ትምህርት ቤት የበኩላቸውን ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል። ለምሳሌ አስተማሪዎችን በማሰልጠን፣ መምህራንን በመመደብና የተለያዩ ለአይነ ስውራን የሚሆኑ ግብዓቶችን በመስጠት ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ።

የመዋዕለ ሕፃናቱ መቋቋም ለእናቶች ልጆቻቸውን በእቅፉ ስላደረገላቸው ተጨማሪ ሥራ እንዲሰሩና የገቢ ምንጫቸውን እንዲያዳብሩ አግዟቸዋል። በዚያ ላይ ልጆቻቸው እውቀትን ሸምተው በስነልቦና ጎልብተው ከቤት ሲደርሱ ደስተኛ እየሆኑላቸው ነው። ነገር ግን በአላቸው መጠነኛ ገንዘብ ብዙ ርቀት ቢጓዙም ቀጣይነቱ ያሳስባቸዋል። ዛሬ ተከፍቶ ነገ እንዳይዘጋ ስጋት አድሮባቸዋል።







ፎቶ ኢዮብ ተፈራ

ወይዘሮ ትዕግስት ካሳ

ትምህርት ቤቱ እንደ ጀማሪነቱ መንግስት ማየት ካልቻለ በስተቀር ብዙ ችግሮች ያሉበት ነው። ሕጻናት በመሆናቸው ልዩ እንክብካቤን ይሻሉ፤ ከዚያም ባሻገር ብሎ አይነ ስውርነት ሲጨመርበት ደግሞ ከዚህ በላይ ብዙ ድጋፍ ይፈልጋሉ። በትምህርት ብቻ ቢነሳ እንደማንኛውም ተማሪ ደብተርና እስኪርብቶ ተገዝቶላቸው በቃ ተማሩ የሚባልበት አይደለም። በቦታም ደረጃ እንደማንኛውም ተማሪ በጠባብ ክፍልና ግቢ ውስጥ የሚማሩ ሊሆኑ አይችሉም። እንደፈለጋቸው የሚንቀሳቀሱበትና አቅጣጫን የሚለዩበት ሰፊ ቦታና ክፍል ያስፈልጋቸዋል።

አይነስውራን ተማሪዎች በአንድ መምህር ክትትል የሚደረግላቸውና የሚማሩም አይደሉም። አይነስውርነት እየነኩ ማስተማርን ይጠይቃል። ስለዚህም የመምህር ተማሪ ጥምርታው ከዚህ የተለየ መሆን አለበት። እናም አምስት መምህራንን ቀጥሮ ማስተማሩ በራሱ ወጪውን ከፍ ያደርገዋል። ከዚያም በተጨማሪ አይነ ስውር ሆነው የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆችም አሉና እነርሱን ለማገዝ አልተቻለም። ተጨማሪ ቴራፒ ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን ለጊዜው እየተሰራ ያለው አይነ ስውርነታቸው ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ነው። እናም ይህንን ያማከለ ትምህርት ለመስጠት ልዩ ቴራፒ የሚሰጡ አካላት ቢደግፉት ይላሉ መስራቿና ዳይሬክተሯ ወይዘሮ ትዕግስት።

አሁን በአሉበት ደረጃ በቃል የሚማሩትን ትምህርት አጠናቀው ወደ ተግባር እየገቡ ነው። ነገር ግን በግብዓት አለመሟላት ምክንያት ይህንን ለማድረግ ያስቸግራል። ምንም ተግባር ውስጥ የሚያስገባቸው ቁሳቁስ የለም። እናም በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሆኑም ያስረዳሉ። ለምሳሌ፡ - ስሌት፣ ስታይለስን የመሳሰሉ መጻፊያዎቹ እና የተለየ ወረቀት ያስፈልጋቸዋል። ስለሆነም ትምህርት ቢሮና ትምህርት ሚኒስቴር ቢያየንና ቢያግዘን ይላሉ ወይዘሮ ትዕግስት።

አይነስውር ተማሪዎች በስነልቦናም ከአሁኑ ጀምሮ መታገዝ አለባቸው። ምክንያቱም ከዚህ ሲወጡ የሚያጋጥማቸው ነገር የተለየ ነው። በተለይም እንደ ሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ብዙ ነገሮች መሰናከል ይሆንባቸዋል። እናም የቻለ ሁሉ ማገዝ ይኖርበታል። በተለይ መንግስት ከመምህራን ስልጠናና ቅጥር ጀምሮ በብዙ መንገድ ማገዝ ቢችል መልካም ነው ባይም ናቸው። እኛም ጅማሮው መልካም ነውና ቀጣይነቱ ላይ ትኩረት ተደርጎ ከተሰራ ለሀገር የሚተርፍ ሃሳብ ነውና ይህንን ፋና ወጊ ትምህርት ቤት ማገዝ ከሁሉም አካላት ይጠበቃል የሚለው መልዕክታችን ነው። ሰላም!!

# ሰላም፣ አንድነት እና ልዕልና - በሀጂ አወል አርባ አንደበት

ሙሉቀን ታደገ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስለኢትዮጵያ መድረክ በአፋር ብሔራዊ ክልል ባዘጋጀበት ወቅት፤ የክልሉ ፕሬዚዳንት ሃጂ አወል አርባ አፋር ላይ መገናኘት ማለት በሉሲ ምድር መገናኛት ነው። በተለይም ደግሞ ስለሰላም ፣ አንድነት እና ልዕልና ለመወያየት በሉሲ መንደር መገናኘት ልዩ ነገር ነው በማለት ነው ሀሳብ መስጠት የጀመሩት።

ሀጂ አወል አርባ እንዳሉት ፤ በዚህ ምድር ላይ ትልቁ ባንክ የሃሳብ ባንክ ነው። በመድረኩ የተነሱ ስለሰላም፣ አንድነት እና ልዕልና በሁሉም የኢትዮጵያ ቤተሰብ ጆሮ መድረስ ይገባዋል። አሁን ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የናፈቀው ሰላም እና ሰላም ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ አሁን ላይ የራሱን ስራ በሚያከናውንበት ወቅት አፋር ሰመራ ላይ ስለሁሉም ኢትዮጵያዊ ሰላም እድገት፣ አንድነት እና ልዕልና ውይይቶች እየተካሄዱ ናቸው። ውይይቶች በቀላሉ ችግሮችን መቅረፍ ስለሚያስችሉ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንደዚህ አይነት ልምዶችን ሊለማማድ ይገባል።

ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎችን ያካተተ ሰላም፣ አንድነት እና ልዕልና ላይ ያተኮረ ውይይት እንደቀላል የሚታይ አይደለም። ለአስተሳሰብ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አለበት የሚሉት ሃጂ አወል ፤ ሀገር የምትፈርሰው አስተሳሰብ ሲፈርስ ነው። በሌላ አነጋገር ሀገር የምትገነባው አውንታዊ የለውጥ አስተሳሰብ ሲኖር ነው። ሀገር የምትገነባው አስተሳሰባችንን በአውንታዊ መልኩ ስንገነባ እና መቀየር ሲቻል ብቻ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ትልቁ ነገር ሰላም ነው። ይህንን ካልን የሰላም ምንጩ የሚገኘው ከየት ነው? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። የምንጠብቀው ከማንስ ነው? በሚሉት ነጥቦች ላይ መግባባት ያስፈልጋል ይላሉ። ከፈጣሪ ምርጥ ስሞች ውስጥ አንዱ ሰላም ነው። ፈጣሪ ራሱን ሲያስተዋውቅ «ሰላም ነኝ» ብሏል። ጀነትም ደግሞ የተሰየመችው በሰላም ነው። ፈጣሪም «ቀጣዩ ጀነት የሰላም ምድር ነው » ብሏል።

እንደ ሃጂ አወል አርባ ገለጻ፤ ሀገርን ከአንድ ቤተሰብ ጋር አመሳስሎ መመልከት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሀገር ማለት ሰው ነው። ሰው የሌለበት መሬት ትርጉም የለውም። የሰው መሰረት ደግሞ ቤተሰብ ነው። መጀመሪያ ሰላም የሚገኘው ለራስ በሰጠው ልክ ነው። ሰላም ለሌሎች ለመስጠት መጀመሪያ ለራስ ሰላም መሆን ተገቢ ነው። ውስጣዊ ሰላም ሊኖር ይገባል። ከዚያ ቀጥሎ ለሌሎች ሰዎች ሰላምን መስጠት ይቻላል። መጀመሪያ ለማን ? ከተባለ መልሱ ለቤተሰብ ይሆናል።

አንዳንድ ሰዎች ቤተሰባቸውን መምራት አቅቷቸው እንዲሁ በስሜት ከባድ ሃላፊነት የሚጠይቀውን ሀገር የመምራት ኃላፊነት ካልሰጣችሁኝ ሲሉ ይስተዋላሉ። ይህ ልክ አይደለም። ቤተሰቡን መምራት ያልቻለ እንዴት ሀገሩን ሊመራ ይችላል? ሀገር ለመምራት መጀመሪያ ራስን የመግዛት ፈተናን ማለፍ ያስፈልጋል። ራሱን የገዛ ሰው ቀጥሎ ቤተሰብ መምራት የሚባለውን ፈተና ተፈትኖ በማለፍ ለቤተሰቡ እንከን የማይወጣለት ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ወይም ንጉስ ሆኖ ማሳየት አለበት። ምክንያቱም ትዳር ከባድ ኃላፊነት ነው። ቤተሰብ ሰላም ከሆነ ሀገርም ሰላም ይሆናል። ኢትዮጵያ ሰላም የምታድርው መቼ ነው ? ተብሎ ከተጠየቀ መልሱ ሁሉም ቤተሰብ ሰላም ያደረ ዕለት ነው በማለት ሰላምን ከየት ማግኘት እንደሚቻል ያስረዳሉ።

እንደሀጂ አወል ገለጻ፤ የሀገረ መንግስት ግንባታ በጽኑ መሰረት ላይ ለማስቀመጥ እና በዘላቂነት ሰላምን ለማምጣት የሀገር አንድነት አስፈላጊ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። ነገር ግን የሀገርን አንድነት ለማምጣት ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ለህዝብ አንድነት ነው። ምክንያቱም ሀገር አንድ መሆን የሚችለው ህዝቡ አንድ ሲሆን ብቻ ነው።

በቅርቡ ተከስቶ የነበረውን የሰላም ዕጦት ብንመለከት ለተፈጠረው ችግር ዋነኛው ምክንያት የሀገር አንድነት አለመኖሩ ሳይሆን የህዝብ አንድነት ስላልነበረ ነው። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው የህዝብ አንድነት የሌለው ሀገር የሀገር አንድነት ቢኖረውም ከመፍረስ አይድንም። በእነዚህ አራት ዓመታት በሀገራችን ተከስቶ ለነበረው ችግር ሌላው ምክንያት የመመራት ልምድ አለመኖር ነው። ይህም ሰላማችንን አናግቶ ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎናል። ስለሆነም በአንድ ሀገር ሰላም ማምጣት ከተፈለገ ማንኛውም ሰው መመራትንም አብሮ መልመድ ያስፈልጋል።


ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

መመራት ምንም ማለት አይደለም። መምራትም በቋሚነት የሚወሰድ አይደለም። በጥሩ ሁኔታ ህዝብን ካገለገልኩ እና ከመራሁ መሪ ሆኜ ልቀጥል እችላለሁ። ካልሆነ ግን ቦታውን ለመልቀቅ እገደዳለሁ። ምክንያቱም ሀገር የጋራ ሃብት ነው። በአጠቃላይ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት እኛ ኢትዮጵያዊን እንደ ሀገር መልመድ ያለብን ነገር መመራትን ነው።

ሌላው ሰላምን ለማምጣት ከሚረዱ አብይ ጉዳዮች መካከል መናበብ፣ መከባበር ነው። ቤተሰብ ቤተሰብ የሚሆነው ሲከባበር እና መናበብ ሲችል ነው። መናብበ እና መከባበር ካልተቻለ ግን በቤተሰብ ውስጥ ሰላምን ማምጣት አይቻልም። በሀገር ደረጃም ተመሳሳይ ነው። ዘላቂ ሰላምን ማምጣት ከተፈለገ እርስ በርስ መናበብ እና መከባበር ያስፈልጋል።

ሀገር ማለት በአንድ በታሪክ አጋጣሚ በሃይል ወይም በምርጫ ያሸነፈ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ሀብት ንብረት ማለት አይደለም። ሀገር ማለት የጋራ እና የሁሉም ዜጋ ነው። በአጋጣሚ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በአንድ ጊዜ ፤ በአንድ ሰዓት በአንድ ምርጫ ሊያሸንፉ አይችሉም። አንድ ፓርቲ ወይም አካል ብቻ ያሸንፋል። አንድ ፓርቲ ወይም አካል አሸነፈ ማለት፤ ሀገር የእርሱ ብቻ ናት ማለት አይደለም። ስለሆነም በአንድ ሀገር ዘላቂ ሰላም ማምጣት ከተፈለገ አሸናፊም ሆነ ተሸናፊ ፓርቲዎች በመደማመጥ እና በመከባባር ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ግድ ነው።

እንደ ሀጂ አወል አርባ ገለጻ፤ ለሰላማችን እንቅፋት የሆኑ የእርስ በርስ ግጭት፣ አለመደማመጥ፣ መሳሳብ፣ የተለጠጡ ሃሳቦችን የመያዝ እንደዚህ አይነት ነገሮችን በውይይት እና በመግባባት ማለፍ ያስፈልጋል። ሀገር ለመገንባት ሀሳብ ማዋጣት ያስፈልጋል። ሃሳባችንን እያዋጣን ለህዝብ እንዲደርስ ማድረግ አለብን። የሃሳብ ውድድር ላይ ብቻ ጊዜ መግደል ሳይሆን የተወዳደርንበትን ሃሳብ ወደ ተግባር መቀየር ያስፈልጋል።

እንደ ሀገር ሰላም ለማምጣት በህዝብ አንድነት ላይ ትልቅ ስራ መሰራት አለበት። የሀገር አንድነትን አስጠብቀን የሰላም ዘብ መሆን ካልቻልን ህልውናችንን የማናጠናክርበት አንዳችም ምክንያት የለም። ባለፈው ዓመት በሀገራችን ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ ታሪካዊ ጠላቶቻችን አሁን አበቃላቸው፤ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች እያሉ ተዘባብተውብን ነበር። በወቅቱ ከበርካታ ዲፕሎማቶች ጋር ተገናኝቶ የማውራት እድልም ገጥሞኝ ነበር። ዲፕሎማቶቹ በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ የነበራቸው አመለካከት እና በጦርነቱ መጨረሻ ላይ የተመለከቷቸው ነገሮች እና አስተሳሰባቸው እጅጉን የተራራቀ ነው።

በጦርነቱ መጀመሪያ ኢትዮጵያ እንድምትፈርስ ያስቡ ነበር። አሁን ላይ ግን ሁሉም ነገር ተቀይሮ ሲመለከቱ የኢትዮጵያን ታላቅ ሀገርነት ሳይወዱ በግድ ተቀብለዋል። ጠንካራ ህዝብ እንዳላት አምነዋል። እንደውም የኢትዮጵያን ህዝብ እንዲህ ነው ብሎ ፈርጆ ማስቀመጥ አይቻልም ያሉኝም አሉ። የኢትዮጵያን ህዝብ ገምግሞ እንዲህ ነው ብሎ መናገር ከባድ መሆኑን ሲናገሩ እየተደመጡ ነው። ለምን ? ኢትዮጵያዊያን በሰላም ወቅት ውስጣዊ ችግሮች ሊኖርባቸው ይችላል። ከበድ ያለ ሀገራዊ አጀንዳ ሲመጣ ደግሞ አንድም ቀን እንዳልተጋጩ ሳይሆን ወደፊትም አንድም ቀን እንደማይጋጩ ሆነው በአንድነት ጠላትን ለመፋለም ይሰለፋሉ። የሚገርመው የትናቱ አይደለም፤ ለነገም የሚጋጩ አይመስሉም ።

በአፋሮች የተለመደ አንድ አባባል አለ፤ «የራስህ ወገን ወይም ዘመድ በድንጋይ ቢመታህ የመታኝ በኩበት ነው ብለህ ዝም ብለህ እለፈው። ነገሩን አታካብደው፤ አታክረው። በቃ ! በኩበት እንጂ በድንጋይ አልመታኝም፤ ብለህ እለፈው። በአንጻሩ ደግሞ ባዕድ የሆነ አካል በኩበት ቢመታህ አልተረፍኩም! በድንጋይ ነው የመታኝ በል። ለምን ? ምክንያቱም ዛሬ ለሙከራ በኩበት ከመታህ ነገ በከባድ ድንጋይ ወይም ከድንጋይ ከበድ ባለ መሳሪያ ደብድቦ ሊገድልህ ይችላል» በማለት ነው በአንድ አገር ህዝብ መሃል ግጭት ቢኖርም በቀላሉ መታየት እንዳለበት እና የባዕድ አገር ወረራን ግን በቀላሉ ማለፍ እንደማይገባ ያስረዱት።

ከዚህ የአፋሮች አባባል አንድ ነገር መረዳት ይቻላል። አሁን ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እርስ በርሱ መዋደድ እና ገመናውን መሸፋፈን አለበት። ራሱንም ከውጭ ወራሪ ለመከላከል አንዱ ወንድም ህዝብ በኩበት ሲመታ በድንጋይ ነው የተመታሁት ብለን ከጎኑ ልንቆም ይገባል ይላሉ።

ሰላም ማለት ሀገር ነው፤ ሰላም ማለት ፍትህ ነው። ለአንድ ሀገር መንግስት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ፍትህን እና ሰላምን ለማስፈን እንዲሁም የሀገር እና የህዝብን ደህንነት ለማስጠበቅ ነው። መንግስትም መንግስት የሚሆነው ሰላምን፣ ፍትህን እና ደህንነትን ማረጋገጥ ሲችል ነው። ህዝብ ሰላም ከሆነ ሀገር ሰላም ይሆናል። መንግስትም ሰላም ይሆናል። ከዚህ አንጻር አስበን ከተንቀሳቀስን እና ከሰራን በሀገራችን ሰላም እና ደህንነት ከማስጠበቅ ባለፈ ለጎረቤት ሀገራትም በሁለንተናዊ መልኩ መርዳት እንችላለን ይላሉ።

አሁን ላይ ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ሰላማችንን እና ልማታችንን ሊያደናቅፍ የሚችል ነገርን ወደ ጎን በመተው የኢትዮጵያዊያን ግንባር ቀደም ዓላማ የሆነውን ልዕልና እና ብልጽግና ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። አጀንዳችን መሆን ያለበት የኢትዮጵያ ልዕልናን ለማረጋገጥ ሌሊት እና ቀን እጅ ለእጅ ተያይዞ መስራት እንጂ በተቃራኒ አቅጣጫ መሳሳብ መሆን የለበትም።

የበርካታ ሀገራት ታሪኮች እንደሚያመላክቱት ከአስከፊ ጦርነት ወይም ከእርስ በእርስ ግጭት በኋላ ሀገራቸውን ከፍታ ላይ ማስቀመጥ ችለዋል። ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያት ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ከማንም ሳይጠብቁ ከእኔ ምን ይጠበቃል? የእኔ ድርሻ ምን መሆን አለበት? ብለው መስራት ስለቻሉ ነው። ኢትዮጵያዊያንም የእነዚህን ሀገራት ተሞክሮ በመውሰድ ኢትዮጵያ ያለእኔ ተሳትፎ ጎደሎ ናት ብሎ በማሰብ ለኢትዮጵያ እድገት እና ልዕልና ማንኛውም ዜጋ የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል። ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠርኩት ለኢትዮጵያ ልዕልና የበኩሌን እንዳበረክት እንጂ ያለምክንያት አይደለም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ለዚህም ራስን

# ወቅታዊ

ማዘጋጀት ይገባል።

በሀገራችን ተፈጥሮ በነበረው ግጭት ወቅት ማንኛውም አፋር ብትጠይቁት ኢትዮጵያ ማለት እኛ አፋሮች ነን ብሎ ይመልሳል። ከዚያ ኢትዮጵያ ደግሞ ማንነቷ ተከብሮ እንድትኖር መከላከያ ያስፈልጋል በሚል እንደአፋር መግባባት ተቻለ። በዚህም መከላከያ በሁሉም ቦታ ማድረስ ስለማይችል፤ ሁሉም የአፋር ህዝብ እኔ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ነኝ ብሎ ማሰብ እንዲችል ተደረገ። የአፋርን ህዝብ እያንዳንድህ ጄኔራል ነህ! ይህን ተቀበል ብለን ተማመን። በዚህም ሁሉም አፋር በፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ቦታ ላይ ራሱን ቁጭ አደረገ፡፡

በዚህም መተማመን ላይ ተደረሰ። ከዚያ በኋላ ስለመከላከያ ሌላ ነገር ማውራት አቆምን። በዚህም ዋናው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት የአፋር ሶስት ወረዳዎችን ሲሸፍን ሌላውን የቀረውን የጦር ቀጠና የተሸፈነው በአፋሮች ነበር። ምክንያቱም እኛ አፋሮች ቀድመን ራሳችን መከላከያ ነን ብለን ስለወሰን፤ በዚህም መላውን አፋርን ከችግር መከላከል ቻልን። ኢትዮጵያንም ማዳን ተቻለ።

ኢትዮጵያዊያን ሁላችንም ለጋራ ሰላም ለጋራ እድገት እና ልዕልና ከመቆም ውጭ ሌላ ምንም አማራጭ የለንም። በአንድ ወቅት ሁለት ጓደኛሞች ነበሩ። አንደኛው አውንታዊ ሃሳብ ይዞ ወደ እድገት እና ልዕልና ሊያመራው ወደሚችል ስራ ውስጥ ይገባል። ከዕለታት አንድ ቀን ይህ ማድረግ የፈለገው ሰው እጅግ አድካሚ እና ጠንካራ የፍየል በረት ይሰራል። ይህ በእንዲህ እያለ ሁለተኛው ሰው ግን አንደኛው ሰው በዚህ ልክ እየለፋ ዝም ብሎ ይመለከተው ነበር ። መጨረሻ ላይ ግን ስራ ሳያግዝ የቆየው ጓደኛ የትጉሁን ሰው ግድግዳ ተጠቅሞ ሌላ በረት ሰራ። መጀመሪያ ላይ ያለገዘከኝን መጨረሻ ላይ ግን የእኔን ግድግዳ ተጠቅመህ እንዴት በረት ትሰራለህ ? ብሎ ጠየቀው። ምንም ሳያግዝ ግድግዳ የሠራው ሁለተኛው ሰው ምን አገባህ? ሲል መለሰለት።

የመጀመሪያው ሰውዬ በሁለተኛው ሰውዬ መልስ ሳይናደድ ለመሆኑ በረቱን የሰራኸው ለምንድን ነው? ሲል ጠየቀው። ሁለተኛው ሰነፍ ሰውዬም መጀመሪያ በረቱን የሰራኸው አንተ ስለሆንክ በረቱን ለምን እንደሰራኸው ንገረኝ ይለዋል። መጀመሪያ በረት የሰራው ሰውዬም በረቱን የሰራሁት በርካታ ፍየሎችን ላረባበት ነው ብሎ ይመልሳል። ይህ ሰው በአውንታዊ አስተሳሰብ ራሱን ለእድገት እና ልዕልና እያዘጋጀ ነበር።

መጀመሪያ በረት የሰራው ሰው ሁለተኛውን በረት የሰራውን ሰው አንተስ የእኔን በረት ተጠቅመህ በረት የሰራኸው ለምንድን ነው? እቅድህ ምንድን ነው? ብሎ ይጠይቀዋል። እኔ እንደ አንተ በርካታ ፍየሎችን ማርባት አልፈልግም። እኔ በዚህ በረት ውስጥ ማርባት የምፈልገው በጣም ትላልቅ የሆኑ ወደ 30 የሚደርሱ ቀበሮዎችን ላራባበት ነው ብሎ ይመልስለታል።

ፍየል ለማርባት በጎ አስተሳሰብ ይዞ መጀመሪያ በረት የሰራው ሰውዬም ኧረ አላህን ፍራ እንዴት ፍየል ለማርባት አቅጄ ከሰራሁት በረት ጎን ቀበሮ ለማርባት ታስባለህ ? ቀበሮ እና የፍየል እርባታ በታሪክ አጋጣሚ በአንድ አካባቢ ተደርጎ አያውቅም። እባክህ ቀበሮ ማርባቱ ይቅርብህ ይለዋል። ነገር ግን አሉታዊ አስተሳሰብን በጭንቅላቱ የከተተው ግለሰብ ምን አገባህ? እኔ የተመቸኝ ቀበሮ ማርባት ነው ? ቀበሮ አረባለሁ ብሎ መለሰ።

ይህን ተከትሎ ሁለቱ ሰዎች ወደከፋ ጠብ ውስጥ ይገቡና አንገት ለአንገት ይያያዛሉ። ይህ በእንዲህ እያለ አንድ ሽማግሌ ወደቦታው ይደርሳል። ሽማግሌውም አንገት ለአንገት ተያይዘው የነበሩትን ሰዎች አላቀው የጸባቸውን መነሻ ምን እንደሆነ ሁለቱንም ይጠይቃሉ። መጀመሪያ በረት የሰራው እና አውንታዊ አስተሳሰብ ይዞ ፍየል ለማርባት የተነሳው ሰውዬ ‹‹ምን መሰልዎት አባቴ፤ እኔ አንድ ሰው ከሰራ እና ከበረታ ወደሚፈልገው ልዕልና መቀየር ይችላል ብዬ አስቤ ይህን የሚመለከቱትን በረት ከፍተኛ የገንዘብ እና የጉልበት ውጭ አድርጌ ገነባሁት። እኔ በረቱን ስሠራ ይህ ሰው መጀመሪያ በእኔ እየሳቀ እና እየቀለደ ምንም ሳያግዘኝ ተኝቶ ሲመለከተኝ ነበር፤ ብሎ ጀምሮ … የጸባቸው መነሻ የሆነውን ጉዳይ ለሽማግሌው ካስረዳ በኋላ ይህ ሰው ግመል፣ ወይ ፍየል ወይ ከብት ማርባት ይችላል ግን እንዴት ፍየል ለማርባት ከሳብኩበት ቦታ ቀበሮ አረባለሁ ይላል? ቀበሮች እና ፍየሎች ጎን ለጎን ካለ በረት ከተቀመጡ ቀበሮዎቹ በአንድ ሌሊት ፍየሎቼን ጨርሰው ይበሉብኛል፡፡›› ሲል ተናገረ።

ሽማግሌውም ቀበሮ አረባለሁ ያለውን ሰውዬ ይሄማ ልክፍት ነው? አሉት። ቀበሮ አረባለሁ ያለው ሰውዬም የምን ልክፍት ነው የሚያወሩት? ሲል ሽማግሌውን ጠየቀ። ሽማግሌውም ልጄ በሰይጣን ክፉኛ ተለክፈሃል፤ ቀበሮ የሚበላ ስጋ የለውም፤ የሚጠጣ ወተት የለውም ታዲያ ቀበሮ አረባለሁ ማለት ከሰይጣንንት ልክፍት በቀር ምን ሊባል ይችላል? ብለው ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት። ቀበሮ አረባለሁ ያለው ሰውዬ በቃ እኔ የተመቸኝ ቀበሮ ማርባት ነው ብሎ በአቋሙ ጸና።

ሽማግሌውም ደግመው ይህ አካሄድህ የልክፍት ነው አሉት። ታዲያ ልክፍት ከሆነ ለዚህ ልክፍት መድሃኒቱ ምንድን ነው? ሲል ቀበሮ አረባለሁ ሲል የነበረው ሰውዬ ሽማግሌውን ጠየቀ። ሽማግሌውም የልክፍቱ ፍቱን መድሃኒቱ ቁጭ ብሎ መወያየት ነው ሲሉ መለሱለት። ሽማግሌውም ቀጥለው ኑ ቁጭ በሉ እና ስለችግሩ እንወያይ ሲሉ ሁለቱን የተጣሉ ወገኖች ቁጭ እንዲሉ አደረጉ።

በውይይታቸውም ይህ ሰው ቀበሮ እንዲያረባ ያደረገው ምንድን ነው ? ብለው በጥልቀት ተነጋገሩ። ሰውዬው ለረጅም ጊዜ በጥፋት አስተሳስብ ውስጥ ከቆየ ጥፋቱን እና ክፋቱን እንደመልካም ነገር እንደሚቆጥር ተግባቡ። ቀበሮዎች ቀበሮ ሆነው የሚታዩት ለፍየል አርቢው እንጂ በክፋት ለአመታት ለኖረው ለቀበሮ አርቢው ግን ቀበሮዎችን እንደ ፍየሎች እንደሚቆጥራቸው ተገነዘቡ። ለምን የጥፋት እና የክፋት አካሄዱ ለበርካታ አመታት ስላደረገው ጥፋቱ እና ክፋቱ ተመችቶታል። ጥፋቱ ደስ ይለዋል። ሰይጣን ሸልሞታልና። በመጨረሻም ሁለቱ የተጣሉ ሰዎች ሽማግሌው ባመቻቸው የውይይት መድረክ መስማማት ላይ ደረሱ በማለት በዚህ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ምንም አይነት ችግር በውይይት መፈታት እንደሚቻል ሀጂ አወል አስተማሪ በሆነው ተረት ሃሳባቸውን ገለፁ።

ሀጂ አወል ደጋግመው እንደሚሉት ሰላም እንዲሁ አይገኝም። ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ በመሳሪያ አፈሙዝ ከማሸነፍ ይልቅ በውይይት አሸናፊ ሆኖ መውጣት ይመረጣል። ለምን ? በአፈ ሙዝ ማሸነፍ ዛሬ ላይ የተሸነፈው ሰው ነገ ላይ ጉልበት ባገኘ ወቅት አሸናፊውን ለመበቀል አፈሙዝ ይዞ መምጣቱ የማይቀር ነው። ስለሆነም ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ውይይት ከጠመንጃ አፈሙዝ የበለጠ ዋጋ ያለው መሆኑን ሁሉም ሰው ሊገነዘብ እንደሚገባ ያሳስባሉ።

የሰላምን ዋጋ ለመግለጽ ከባድ ነው። ስለሰላም ዋጋ ለመረዳት ከፈለግን በቅርቡ በሀገራችን ከተፈጠረው የሰላም እጦት ጋር ተያይዞ ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደ መቀሌ የተደረገውን የአውሮፕላን በረራ ብቻ መመልከቱ በቂ ነው። እንደሚታወቀው በሀገራችን የነበረው የሰላም መደፍረስ ተከትሎ በመቀሌ እና በአዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች ግንኙነታቸው ተቋርጦ ነበር። ይሁንና አሁን ላይ የተፈጠውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ አውሮፕላን ወደ መቀሌ በረራ ባደረገ ጊዜ በአሉላ አባ ነጋ ኤርፖርት የነበረው ደስታ፣ ለቅሶ እና ሌሎች ሁነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖርን መቀሌ እንደ ጨረቃ እርቃን እንደነበር አሳይቶናል። ለሁለት ዓመታት ተለያይተው የነበሩ ሰዎች ሲገናኙ ከሞተ ሰው ጋር እንጂ በሕይወት ካለ ሰው ጋር የተገናኙ አይመስልም ነበር። ይህም ሰላም ለሰው ልጆች ያለውን ውድ ዋጋ ምን ይህል እንደሆነ ያመላክታል።

ጀግና መሪ ማለት ወደ ጦርነት ከመግባቱ በፊት ጦርነቱ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ጥፋቶች ተንብዮ ሀገርንም ህዝብንም ከጥፋት የሚያድን ነው። የመጀመሪያውን የጦርነት ሁነት አይቶ በመጀመሪያው ሁነት የሚደሰት አይደለም። ጀግና ማለት የመጀመሪያውን ተመልከቶ የመጨረሻውን የሚተነብይ ነው። በአፋር ሁለት ጎሳዎች ተጣልተው ለሰላም በተቀመጡ ጊዜ የአፋር ሽማግሌዎች ሰላም የሚፈልገውን እና የማይፈልገውን ጎሳ የሚለዩበት የራሳቸው መለያ መስፈርት እንዳላቸውም ያብራራሉ።

ሰላም የሚፈልግ ጎሳ የትናንቱን በዜሮ እናባዛው እና ለነገ እናስብ፤ ለአዲስ ሕይወት እንዘጋጅ ይላል። በዚህም ከልቡ ሊታረቅ መፈለጉን ያመላክታል። ሁለተኛው መታረቅ የማይፈልግ ጎሳ ግን የወደፊቱን አጨልሞ ይመለከታል። ለመታረቅ ሽማግሌ ፊት ቆሞ ለእርቅ ከመቀመጡ በፊት የነበሩ ጥፋቶችን እና ቁስሎችን በተደጋጋሚ ያነሳል። ለነገ የሚያስብበት ጊዜ ፈጽሞ የለውም። ይህን ተከትሎ ሽማግሌዎች የትናትናውን እያነሳ የወደፊቱን መመልከት የተሳነው ጎሳ መታረቅ እንዳልፈለገ ፤ ለሰላም እጁን እንዳልዘረጋ በደንብ ይገነዘባሉ፡፡



የአፋር ሽማግሌዎችም ሰላምን ለማምጣት ከትናንትናው ይልቅ ለነገ ማሰብ እንደሚያስፈልግ ትናንትን እያነሳ ለሚከራከረው ጎሳ ይመክራሉ፤ ይዘክራሉ። በዚህም ሁለቱንም ጎሳዎች ወደ ሰላም ያመጧቸዋል። እኛም እንደሀገር ሰላም መሆን ከፈለግን በፊት የነበሩ ቁስሎችን በዜሮ አባዝተን ለነገው ማሰብ ያስፈልጋል ሲሉ ቂምና ቁርሾ የነገን ሰላም እንደማያመጣ ይናገራሉ።

ሌላው በመድረኩ በሀጂ አወል የተብራራው አንድነት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ነው። ስለ አንድነት ሲያስረዱ አንድ የአፋር ተረትን ተጠቅመው ነበር። በአንድ ጎጆ ውስጥ የሚኖሩ ወፎች ነበሩ። ወፎቹ ጎጇቸውን የሰሩት ዛፍ ላይ ነበር። ወፎች ዛፉ ላይ ጎጇቸውን ሰርተው እየኖሩ አንድ ቀን ጎጇቸው ውስጥ እያሉ እርስ በርሳቸው ይጣላሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ አውራ ግመል ወደዛፉ ተጠግቶ የጎጆዋን ሳር ለመብላት ፈልጎ ጎጆዋን ወደ አፉ አስገባ ። በጎጆዋ ውስጥ ጸብ ላይ የነበሩ ሁለቱ ወፎችም ከጎጇቸው ጋር በግመሉ ተበሉ።

ወፎቹ ሰላም ቢኖራቸው እና ቢተባበሩ ግን አይደለም በግመሉ ሊበሉ ይቅርና ጎጇቸውንም አያስደፍሩ ነበር ። እኛም ጎጇችን ውስጥ እርስ በርስ ስንበላላ እንደግመሉ ከውጭ ለመጣ ጠላት ሲሳይ እንዳንሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። አንድ ስንሆን ሁሉም ያከብረናል። የምንሰራው ሥራም ውጤታማ ይሆናል። ስንበታተን ግን ማንም እየተነሳ ይጫወትብናል። ይህን ለመገንዘብ በሀገራችን ለተወሰነ ጊዜ በነበረው የሰላም እጦት ወቅት ያየናቸው ምልክቶች ከበቂ በላይ አስተማሪ ናቸው።

ሰላም ሲባል ከሁሉም በላይ ፍትህ፣ የህግ የበላይነት፤ ስርዓት ማስከበር ማለት ነው። ምክንያቱም የህግ የበላይነት እና ፍትህ በሌለበት ሰላም ከየትም አይመጣም። ጠንካራ ሀገር እንዲሁ መፍጠር አይቻልም። ጠንካራ ሀገር ለመፍጠር መጀመሪያ ጠንካራ የስራ ባህል፣ አንድነት ያለው ህዝብ ያስፈልጋል። ከዚያ ቀጥሎ ጠንካራ ኢኮኖሚ ያስፈልጋል። ከጠንካራ ኢኮኖሚ ቀጥሎ ጠንካራ የሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ ጠንካራ ፖሊስ፣ ጠንካራ የደህንነት ተቋም መገንባት ያስፈልጋል። በአጠቃላይ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ላይ ትልቅ አቅም መገንባት ያስፈልጋል። ከዚያ የሚከበር እና የሚፈራ ሀገርን መፍጠር ይቻላል።

ታላቅነት የሚረጋገጠው አንድነት ሲኖር ነው። የአንድ ወይም የሁለት ክልል ታላቅነት አንድን ሀገር ሊያሻግር አይችልም። በአፋር ክልል የአንበጣ ወረረሽኝ፣ ጎርፍ እና ሌሎች ችግሮች መከሰታቸው በውጭ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ፣ በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ጡረተኞች ፣ አካል ጉዳተኞች በአጠቃላይ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከአፋር ጋር በአንድነት መቆማቸውን ያየንበት ነው። በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያዊነት ኩራት መሆኑን አይተናል። የአንድነትንና የኢትዮጵያዊነትን ልክ አይተናል።

አፋር ጀግና እየተባለ ሲወደስ ይሰማል። አፋርን ጀግና ያደረገው ኢትዮጵያዊ በአንድነት ከጎኑ ስለቆሙ ነው። አሁንም ህብረ ብሄራዊ አንድነታችን ተጠናክሮ እንዲቀጥል በደንብ መስራት አለበት። ልዕልናችንም ለማስቀጥል የተጀመሩ የልማት ስራዎችን መጨረስ እና ሌሎች አዳዲስ የልማት ስራዎችን መጀመር ያስፈልጋል።

በሚቀጥለው ስለኢትዮጵያ ውይይት መቀሌ ተገናኝተን ስለሰላም ፣ አንድነት እና ልዕልና መምከር ይጠብቀብናል። ገጥሞን የነበረውን የሰላም ችግር በውይይት እየፈታን ነው። አሁንም ይህን አጠናክረን መቀጠል አለብን በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል።

# ዓለም አቀፍ




## በቻይና በአንድ ወር 60 ሺህ ሰዎች በኮቪድ ሕይወታቸው ማለፉ ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ቻይና በአራት ሳምንታት ብቻ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ 60 ሺህ ሞት መመዝገቧን ይፋ አደረገች።

ቻይና ያመነችው ይህ ከፍተኛ የሞት ቁጥር የተመዘገበው ጥብቅ የኮቪድ-19 ክልከላዎችን ካነሳች በኋላ ባሉት ሳምንታት ነው።

የበሽታው መነሻ መሆኗ የምትታመነው ቻይና በኮቪድ የሚያዙ እና የሚሞቱ ሰዎችን ትክክለኛ አሃዝ ይፋ አታደርግም ተብላ በምዕራባውያን ትወቀሳለች።

ቤይጂንግ ግን በበሽታው የሚያዙ እና የሚሞቱ ሰዎች ቁጥርን በተመለከተ የምታወጣው አሃዝ ትክክለኛ መሆኑን ስትገልጽ ቆይታለች።

ቻይና ታኅሣሥ ወር ውስጥ 59 ሺህ 938 ከኮቪድ ጋር የተያያዘ ሞት መመዝገቧን ይፋ አድርጋለች።

ከሟቾቹ መካከል አብዛኛዎቹ ከ80 ዓመት በላይ የሆናቸው እና የቀድመ የጤና ቀውስ ያለባቸው ናቸው ተብሏል።

5 ሺህ 503 ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ባጋጠመ የመተንፈስ ችግር ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን 54 ሺህ 435 ሰዎች ደግሞ የኮቪድ ሕመም ከዚህ ቀደም ከነበረባቸው በሽታ ጋር ተደራርቦ ሞት አስከትሎባቸዋል ብለዋል የቻይና የጤና ባለስልጣናት።

ይህ የሞት መጠን የተመዘገበው በጤና ተቋማት ብቻ በመሆኑ የሟቾች ቁጥር አሃዝ ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል።


ቻይና ከጥቂት ሳምንታት በፊት በቫይረሱ ሕይወታቸውን ያጡ ብላ የምትፈርጀው በኮቪድ-19 ምክንያት የመተንፈሻ ሥርዓታቸው መሥራት በማቆሙ ሕይወታቸው ያለፈውን ብቻ ነው።

የዓለም ጤና ድርጅት ግን ይህ አመዳደብ "እጅግ ጠባብ" ሲል ተቃውሞታል።

የቻይና የጤና ባለስልጣናት በተለይ በአገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች በሚያደርጉት የኮቪድ ክትትል እና ቁጥጥር እንዲሁም የበሽታው ስርጭት ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

## በባይደን መኖሪያ ቤት ተጨማሪ ምስጢራዊ ሰነድ ተገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምስጢር የያዘ ባለ አምስት ገጽ ሰነድ ዴልዌር በሚገኘው የፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የግል መኖሪያ ቤት መገኘቱን ዋይት ሃውስ አስታወቀ።

የፕሬዚዳንቱ ጠበቃ ሪቻርድ ሱበር ተጨማሪ ሰነዱ እንደተገኘ በፍጥነት ለፍትሕ ቢሮ ማስረከባቸውን አስታውቀዋል።

ጠበቃው ባይደን በኦባማ አስተዳደር ወቅት ምክትል ፕሬዚዳንት ሳሉ የነበሩ ሰነዶች ናቸው ብለዋል።

በባይደን መኖሪያ ቤት አገራዊ ምስጢር የያዙ ሰነዶች መገኘታቸውን ተከትሎ ምስጢራዊ ሰነድ አያያዛቸውን በተመለከተ ምርመራ የሚያደርግባቸው ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሟል።

ፖለቲከኞቹ ፕሬዚዳንቱ ሆነ ብለው ምስጢራዊ ሰነዶችን በተገቢው መንገድ አልያዙም በማለት እያብጠለጠሏቸው ይገኛሉ።

በተመሳሳይ በቀድሞ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ መኖሪያ ቤትም አገራዊ ምስጢር የያዙ ሰነዶች መገኘታቸውን ተከትሎ ምርመራ እየተደረገባቸው እንደሆነ ይታወቃል።

ትራምፕ ምርመራ የተጀመረባቸው 'ከባድ ምስጢር' ያሉትን ጨምሮ ከ300 በላይ ሰነዶች ፍሎሪዳ በሚገኘው ማር-አ-ላጎ መኖሪያ ቤታቸው ከተገኙ በኋላ ነው። ሰነዶቹን የፌዴራል ቢሮ መርማሪ ፖሊስ ድንገተኛ ፍተሻ ካደረገ በኋላ ያገኛቸው ናቸው።

በባይደን መኖሪያ ቤት ምስጢራዊ ሰነድ ሲገኝ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም። በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ እና ከጥቂት ሳምንታት በፊት በባይደን መስሪያ ቤቶች እና በግል መኖሪያ መኪና ማቆያቸው ውስጥ ሰነዶች ተገኝተው ነበር።

ሰነዶቹ በፕሬዚዳንቱ መኖሪያ ቤት መገኘታቸው የፖለቲካ ኪሳራ እንደሚያስከትልባቸው ብዙዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው።

በአሜሪካ ሕግ 'ጥብቅ የአገር ምስጢር' የተደረጉ ሰነዶች መቀመጥ የሚችሉት በፌዴራል ቤተ-መዘክር ውስጥ ብቻ ነው።

የባይደን ጠበቃ የፕሬዚዳንቱን ምስጢራዊ ሰነድ አያያዝን በተመለከተ እንዲመረምር ከተቋቋመው ኮሚቴ ጋር ዋይት ሃውስ ተባባሪ እንደሚሆን ገልጸዋል።

በፕሬዚዳት ጆ ባይደን መኖሪያ ቤት ምስጢራዊ ሰነዶች መገኘታቸውን ተከትሎ የፕሬዚዳንቱ ጎብኚዎችን ዝርዝር የያዘው መዝገብ ምርመራ እንዲደረግ የባይደን ተቀናቃኞች እየጠየቁ ነው።

ሪፐብሊካኑ የምክር ቤት አባላት በባይደን መኖሪያ ቤቶች በአንዱ የተገኘው ሰነድ «ብሔራዊ የደኅንነት አደጋ» ነው ሲሉ የጎብኚዎች ስምና ማንነት የሚሰፍርበት መዝገብ ይፋ እንዲሆን ጠይቀዋል።

ዋይት ሃውስ ግን ይህ የሪፐብሊካኑ ጥያቄ ምላሽ ያገኝ እንደሆነ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቧል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

## የፈጠራ ሐሳብ ያላቸውን ዜጎች የማገዙ ጥረት

ተማሪ ይድነቃቸው ተከሉ የ12ተኛ ክፍል ተማሪ ነው። በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ ( Science,Technology, Engineering And Maths (STEM) ስቴም ማዕከል አጋዥነት የፈጠራ ሥራውን ለውድድር አቅርቧል። እርሱ እንደሚለው የፈጠራ ሥራዎች ተጠቃሚ የሚሆኑት ወደ ተግባር ተቀይረው ማሕበረሰቡ ጋር ሲደርሱ ብቻ ነው። ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን እውቀት ብቻ ሆነው ምንም ጥቅም ሳይሰጡ ይቀራሉ። ተማሪ ይድነቃቸው በ2014 ዓ.ም የሳይንስ ቀን በተከበረበት ወቅት የአውቶማቲክ እንጀራ መጋገሪያ በመሥራት በውድድር ላይ ከመሳተፍ አልፎ ተርፎ ተሸልሞበታል። ነገር ግን ሥራውን እውን ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ አናሳ በመሆኑ የፈጠራ ሥራው ማሕበረሰቡ ጋር አልደረሰለትም። በዚህ ተስፋ ያልቆረጠው ተማሪው አሁን ላይ የእሳት አደጋ በሚነሳበት ወቅት ራሱ አስተካክሎ (አጀስትመንት ሰርቶ) እሳቱን የሚያስቆም የፈጠራ ሥራውን ለውድድር አብቅቷል። የፈጠራ ሥራው በሁለት አይነት መልኩ የሚሠራ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ኤሌክትሪኩን በማቋረጥ እሳቱ ወደሌላ ክፍል እንዳይዛመት ማድረግና ግለሰቡ ከተኛ ደግሞ እንዳይታፈንና እንዳይሞትም በሮችን ከፍቶ ጭሱን በማስወጣት እንዲተርፍ የሚያስችል ነው። ሁለተኛው ደግሞ በወተር ፓምፕ አማካኝነት የተነሳውን እሳት ማጥፋት ሲሆን፤ በተለያዩ ቋንቋዎች መጠቀም የሚያስችለን ስርዓት የተቀመጠለት ነው፡፡

ይድነቃቸው እስካሁን በነበረው ጉዞ ከ21 በላይ የፈጠራ ሥራዎችን መሥራት ችሏል። ሥራዎቹ ተመርተው ወደ ሕብረተሰቡ ቢወርድ በርካታ ችግሮችን የሚያቀል መሆኑን በመጠቆም፤ እንደ ሀገር ከተወሰደ በተለይም በክልል ከተሞች አካባቢ ለሚከሰተው የድንገተኛ እሳት አደጋ ፍቱን መፍትሄ የሚሰጥ እንደሆነም ያብራራል። ስለሆነም መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ድጋፋቸውን ለፈጠራ ባለሙያዎች ቢያደርጉ እንደ ሀገር ብዙ ችግሮችን መፍታት እንደሚቻል ይገልጻል፡፡



**የሳይንስ ሙዚየም በተመረቀበት ወቅት**

የፈጠራ ሥራ ባለሙያው ተማሪ አብዱርቃድር ሁሴን ወደ 25 የሚሆኑ ፈጠራ ሥራዎች ያሉት ሲሆን፤ በ2014 ዓ.ም በተካሄደው የፈጠራ ሥራ ውድድር ላይ ‹‹ፉራ›› የሚባል የመኖ ማቀነባበሪያ ሠርቶ ለሽልማት ከመብቃት በሻገር አሁን ላይ ወደ ምርትነት ወይም ወደ ገበያ መቀላቀሉን ያነሳል። የፈጠራ ሥራ ከልጅነቱ ጀምሮ እየሠራበት እንደሆነ የሚያስረዳው የ10ኛ ክፍል ተማሪ አብዱልቃድር፤ ትምህርቱን አምስት ጊዜ አቋርጧል። ይህም የሆነበት ምክንያት የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት የገንዘብ እጥረት የሚያጋጥመው በመሆኑ የቀን ሥራ ለመሥራት ሲል ትምህርቱን በተደጋጋሚ እንዲያቋርጥ ምክንያት ሆኗል። ብዙ ውጣ ውረዶችን ያሳለፈው ተማሪው ችግር ፈቺ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት ብዙ እቅድ እንዳለውም ይገልጻል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም በሀገራችን የተለያዩ ተሰጥኦዎች ያላቸውን ተማሪዎች ተቀብሎ እንደ ፍላጎታቸው ለማስኬድ ከዚህ ቀደም አዳጋች ነገሮች እንደነበር ይገለጻል። ተማሪዎቹ ተሰጥኦቸውን አበልጽገው ወደ ምርትና አገልግሎት ለመቀየር ሲያስቡ የትምህርት ቆይታቸውን ማጠናቀቅ ግድ ይላቸዋል፣ አልያም ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠርላቸው ባክነው ይቀራሉ። አሁን አሁን ግን በመንግስት በኩል እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የትምህርቱን ዘርፍ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። ለአብነት ያህል ለማንሳት ከዚህ ቀደም በኦሮሚያ ክልል በቡራዩ ከተማ አስተዳደር የተመረቀው የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤትም ይህንን ችግር የሚቀርፍ እንደሆነ ነው የተገለጸው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሰባት መቶ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ 93 ሺ ብር ወጪ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም መርቀው መክፈታቸው የሚታወስ ሲሆን፤ ይህ ትምህርት ቤት አንድ ሺ ባለ ልዩ ተሰጥኦ ተማሪዎችን ተቀብሎ የማስተማር አቅም አለው።

ኢትዮጵያ የምትቀየረው፤ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎችን የሚያበረታቱና የሚደግፉ ማዕከላት ሲስፋፉ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቡራዩ የተገነባው ልዩ የተሰጥኦ ትምህርት ቤት የተለየ የፈጠራ ሃሳብና ክህሎት ያላቸው ወጣቶችና ታዳጊዎች ለሀገር ጥቅም ከፍተኛ ሚና እንዲያበረክቱ ያስችላልም በማለት ያስገነዝባሉ። የትምህርት ቤቱ ፕሮጀክት ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በአስር ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ ሲሆን፤ የተመረቀው በአምስት ነጥብ አራት ሄክታር ላይ ያረፈው ፕሮጀክት ነው። ትምህርት ቤቱ የባለተሰጥኦዎች ማደሪያ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የአስተዳደር ህንጻዎች፣ የህክምና ማዕከል፣ መማሪያ ክፍሎችና ቤተ ሙከራዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡

ሌላው ለፈጠራ ሥራ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል የተባለው የሳይንስ ሙዚየም መገንባቱም ለህጻናትና ወጣቶች የፈጠራ ሃሳብ ልምምድና ለፈጠራ እድገት የላቀ ሚና እንደሚኖረው የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሳይንስ ሙዚየም የተሻለች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በልጆች ላይ መሰረት የሚጥል፤ በተለይም የታዳጊና ህጻናት ልጆች የሳይንስና የፈጠራ ህልም እውን የሚሆንበት እንደሆነ ያመላክታሉ። ህፃናት በቴሌቪዥን ሲመለከቷቸው የነበሩ የተለያዩ የሳይንስ መገለጫዎችን በሙዚየሙ በአካል የመመልከት እድል ማግኘታቸው ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነና ሙዚየሙ ህጻናትና ወጣቶች የፈጠራ ሀሳቦችን እንዲለማመዱና እንዲያሳድጉ የሚያስችሉ ማዕከላት አሉት። ይህም የተሻለች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ለሚደረገው ጥረት መሰረት የሚጥል ነው። የሙዚየሙ መገንባት ለከተማዋ ውበትን እንዲሁም ለትምህርት ተቋማትና አጠቃላይ ወጣቶች እውቀትን የሚያጎናጽፍ መሆኑን የተናገሩት ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ናቸው፡፡

# ስፖርት



# ዋልያዎቹ ከወሳኙ ፍልሚያ በፊት ሊያርሟቸው የሚገቡ ክፍተቶች

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በቻን ዋንጫ የመጀመሪያ ጨዋታውን ከትናንት በስቲያ ከሞዛምቢክ ጋር አድርጎ 0ለ0 በሆነ ውጤት አጠናቋል። ዋልያዎቹ በዚህ ውድድር በምድብ አንድ ከአዘጋጇ አልጄሪያ፣ ሊቢያና ሞዛምቢክ ጋር መደልደላቸው የሚታወቅ ሲሆን በውድድሩ ረጅም ርቀት ይጓዛሉ ተብሎ ከሚጠበቁ ቡድኖችም ተጠቃሽ ናቸው። ይሁን እንጂ ከሞዛምቢኩ ጨዋታ በኋላ ዋልያዎቹ በውድድሩ ረጅም ርቀት ይጓዛሉ የሚለው ግምት የመሳካቱ ነገር አጠራጣሪ ሆኗል።

ዋልያዎቹ በዚህ የውድድር መድረክ ለሦስተኛ ጊዜ እንደመሳተፋቸው ካለፉት ሁለት የተሳትፎ ታሪካቸው የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ የሚል እምነት ተጥሎባቸዋል። በተጨማሪም ዋልያዎቹ ባለፈው ግንቦት በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ትልቁን የግብጽ ብሔራዊ ቡድን ከጨዋታ ብልጫ ጋር 2ለ0 ማሸነፋቸው ቻን ላይ የተለየ ትኩረት እንዲሰጣቸው አድርጓል። ምክኒያቱም ያንን አስደናቂ ጨዋታና ድል ፈርኦኖቹ ላይ ማስመዝገብ የቻለው የዋልያዎቹ ስብስብ ከሞላ ጎደል በዚህ የቻን ውድድር ላይ ተካቷል። አማካዩ ሽመልስ በቀለና አጥቂው አቡበከር ናስር በውጪ ሊጎች የሚጫወቱ ተጫዋቾች እንደመሆናቸው በዚህ ውድድር ከዋልያዎቹ ጎን አይሰለፉም። በተረፈ ግን ግብጽን ካሸነፈው ቡድን ዋልያዎቹ ያጡት ወሳኝ ተጫዋች ዳዋ ሆጤሳ ነው። ከዚህ አኳያ ዋልያዎቹ ሞዛምቢክን በቀላሉ ያሸንፋሉ ብሎ ማሰብ ጤናማ ነበር። ያምሆኖ ግን ዋልያዎቹ የምድቡን ቀላል ተጋጣሚ መረብ መድፈር ሳይችሉ ቀርተዋል። ዋልያዎቹ ምናልባትም በዚህ ውድድር የግድ ማሸነፍ ካለባቸው ሞዛምቢክን ነበር። ግን አልሆነም። ይህም በውድድሩ ለመቆየት ያላቸውን እድል ያጠበበ ሲሆን በቀጣይ ሁለት የምድብ ጨዋታዎችም ጫና ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል።



ዋልያዎቹ በሞዛምቢኩ ጨዋታ የበላይነት ቢያሳዩም ኳስና መረብ ማገናኘት አልቻሉም፣

ዋልያዎቹ በሞዛምቢኩ ጨዋታ የነበራቸው እንቅስቃሴ ከቁጥር አንጻር ይገለጽ ከተባለ በኳስ ቁጥጥርና በጨዋታ የበላይነት ጥሩ ነበሩ ብሎ መደምደም ይቻላል። ይሁን እንጂ የገጠሙት እጅግ በጣም የመቀናጀት ችግር ያለበትን ቡድን እንደመሆኑ ግብ ማስቆጠር አለመቻላቸው ዋልያዎቹ ብዙ ችግሮች እንዳሉባቸው አመላካች ነው። ዋልያዎቹ የግድ በውድድሩ ለመቆየት እነዚህን ችግሮች በቀጣይ የምድብ ጨዋታዎች አርመው መገኘት ይኖርባቸዋል።

በቅዳሜው ጨዋታ በተለይም በሁለተኛው ግማሽ ላይ ለቀጣይ ሁለት ጨዋታዎች ዋልያዎቹ ማረም ያለባቸውን ችግሮች ፍንትው አድርገው አሳይተዋል። የአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ቡድን የውሳኔ፣ የጉጉት፣ የጨራሽነት ችግሩን በቀጣይ ጨዋታዎች መቅረፍ አለበት።

የአሰልጣኝ ውበቱ አባተን የተጫዋቾች ምርጫ ማክበር ተገቢ ቢሆንም ቡድኑ በሁለቱ ጨዋታዎች የሚያጣውን ነገር ከሞዛምቢኩ ጨዋታ የግድ መማር ይጠበቅበታል። የዋልያዎቹ ሁለቱ ቀጣይ ተጋጣሚዎች መስመር ላይ የተሻለ እንቅስቃሴ በማድረግ አደጋ መፍጠር የሚችሉ ናቸው። የግማሽ ሜዳ አጠቃቀም አቅማቸው ያደገ ነው። ሩጫዎቻቸው እና ረዣዥም ኳሶቻቸውም ለመከላከል እና ለመቋቋም ይከብዳሉ። ይህ ማለት በሞዛምቢኩ ጨዋታ ከሁለቱ ቀጣይ ተጋጣሚዎች አንፃር ደካማ የነበረውን ሞዛምፒክ ሲገጥሙ የፈጠሯቸውን ስህተቶች እና የአጨራረስ ድክመቶች በቀጣዮቹ ሁለቱ ጨዋታዎች እንዲሁ በቀላሉ የሚታዩ ሳይሆን ዋጋ የሚያስከፍሉ ናቸው።

ግብ ጠባቂው ፋሲል ገብረሚካኤልም ሜዳ ውስጥ ያለውን የዕርጋታና የግል ቁጥጥሩን ማሳደግ አለበት። አንዳንድ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ቡድኑንም የእሱንም የእግርኳስ ዘመን እድገት የሚቀንሱ ናቸው። በተፈጥሮው ጥሩ ግብ ጠባቂ ነው። ነገር ግን የሜዳ ውስጥ አቅሙን ማሳደግ ይኖርበታል።

የዋልያዎቹ ስብስብ ከዛሬ 15 አመት በፊት ይነሳበት የነበረው የአጨራረስ ችግር ዛሬም አብሮት አለ። ቡድኑ እንደፈለገው ኳስ ይነጥቃል ኳስ ያደራጃል በፈለገው ሰዓት የተቃራኒ ቡድን ክልል ውስጥ ይደርሳል፣ የአንድ ሁለት እንቅስቃሴዎቹም ጥሩ ናቸው፣ ነገር ግን ይሄ ኳስ እና መረብን ካላገናኘ ሶስት ሊገኝ አይችልም።

የወዳጅነት ጨዋታ ጥቅሞች ይሄና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ነው። ምክንያቱም ከልምምድ በላይ ጨዋታ የቡድኑን ደካማና ጠንካራ ጎን ያሳያልና።

ሞዛምቢኮች በሁለተኛው አጋማሽ እራሳቸውን ፈልገው አግኝተዋል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ዋልያዎቹ ኳስን መቆጣጠር እንጂ ወደ ጎል ለመቀየር ያላቸው ችኮላ ውጤታማ እንደማያደርጋቸው ተረድተዋል።

በእግር ኳስ ልምድ ወሳኙ ነገር ነው። ለዚህ ነው ልምድ ያስተማራቸውን ተጫዋቾች የየክለብም ይሁን የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞች የሚፈልጓቸው። አሰልጣኝ ውበቱ በጉዳት ቡድኑ ውስጥ የሌሉትን እንደ ዳዋ ሆጤሳ ዓይነት ተጫዋቾች የሚተካ አዲስ ትውልድ መመልከት ያለባቸው ወቅትም አሁን ነው። ይህንንም አሰልጣኙ ነገ በሁለተኛው የምድብ ጨዋታ አዘጋጇ አልጄሪያን በኔልሰን ማንዴላ ስቴድየም ሲገጥሙ አስበውበት ወደ ሜዳ እንደሚገቡ ይጠበቃል።


## ማስታቂያ

“ማዳን ፋውንዴሽን” የተባለ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በባለስልጣን መስሪያቤት የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል:: ተቃዋሚ አካልካለ እስከ ጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን መስሪያ ቤት ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## የስም ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል አለም አቀፍ ፋውንዴሽን የተባለ አገር በቀል ድርጅት ከዚህ በፊት ያልነበረ ሲሆን ከዚህ በታች በተቀመጠው አርማ የሚጠቀም መሆኑን እያሳወቅን

ETHIOPIAN HISTORY & CULTURE
INTERNATIONAL FOUNDATION

ተቃዋሚ ካለ እስከ ጥር 14/2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ሕብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ድረስ ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## ማስታወቂያ

ሰክሰስ የበጎ አድራጎት ማህበር ሲቪል ማህበረሰብ ማህበር አገር በቀል ድርጅት ሆኖ ለመመዝገብ በሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረተ ውክልና በተሰጠው በድሬዳዋ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል:: ተቃዋሚ ካለ ለጥር 8 ቀን 2015 ዓ.ም በድሬዳዋ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 205 ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ይቅረብ::

**ገንዘብናኢኮኖሚ ልማት ቢሮ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ እስቴላ ብሩምሔድ እና በተከሳሾች እነ ጂ-7 ኃ/የተ/የግ/ማኅበር
ኤርኒፖ ጆርጋሊስ
መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎን አውቀው ለ17/05/2015 ዓ.ም. በ8፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው ፌ/ከ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 8ኛ ልዩ ልዩ ፍ/ብሄር 02ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 203 ቀጥታ ክስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

## Invitation for National Competitive Bid
## Bid Ref. No. Re-Bid DBE/NCB/CS/002/2022/23

1. Development Bank of Ethiopia invites interested bidders for the procurement of Consulting Service of Finance and Accounting Practice of the Bank.
2. Interested bidders are required to submit together with their bid documents;

| | |
|---|---|
| i. Renewed Trade License | IV. Tax clearance certificate |
| ii. TIN Certificate | V. Registration Certificate from responsible public body. |
| iii. VAT Registration Certificate | VI. Competence Certificate |

3. Interested bidders may Purchase a complete set of bidding documents beginning from January 16/2023 upon payment of a non-refundable Birr 300.00 (Birr Three hundred only) to Customer Accounts Transaction Service office, Tower II, Ground floor and collect the bid documents from Procurement Directorate, Tower III, 1st floor.
4. Bid shall be accompanied with a bid security ETB 50,000.00 (Fifty Thousand Birr) in the form of C.P.O or unconditional bank guarantee from recognized bank.
5. Bids shall be submitted into the tender box prepared for this purpose on or before February 01, 2023 at 10:00 A.M. at Development Bank of Ethiopia Head Office Tower II, Ground floor.
6. Bids shall be opened in the above mentioned address, on February 01, 2023 at 10:05 A.M. in the presence of bidders and/or their authorized representatives.
7. Interested bidders may obtain further information from DBE Head Office, Procurement, Tower III, 1st floor, Tel. +251 115578088, ext. 364.
8. Bidders should present their Financial and Technical documents separately in sealed envelope.
9. The language of the tender is English.
10. DBE reserves the right to accept or reject any or all bids.

**Development Bank of Ethiopia**